# አዲስ ዘመን

ኢትድ

ማክሰኞ 81ኛ ዓመት ቁጥር 284 ሰኔ 14 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72

ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና 0111 26 23 18

ይዘዙን

ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።

ነገን ዛሬ እንሥራ









# ጥቃት በደረሰባቸው አካባቢዎች ሰላም እና ደህንነትን መመለስ ቅድሚያ የሚሰጠው ተግባር መሆኑ ተገለጸ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- ጥቃት በደረሰባቸው አካባቢዎች ሰላም እና ደህንነትን መመለስ አሁንም ቅድሚያ የምንሰጠው ተግባራችን ነው ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ አስታወቁ።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በማኅበራዊ ትስስር ገጻቸው ባስተላለፉት መልዕክት "በንጹሓን ዜጎች ላይ በሕገወጥ እና በኢ-መደበኛ ኃይሎች የሚደርስ ጥቃት እና መተዳደሪያን ማውደም ተቀባይነት የለውም" ብለዋል።

"ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በቤኒንሻንጉል እና ኦሮሚያ ክልሎች፣ ዋና ዓላማቸው ኅብረተሰቡን ማሸበር ከሆነ አካላት የተፈጸመው የሰው ልጆችን ሕይወት የሚቀጥፍ

ጥቃት በደረሰባቸው... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


አርሾ
ሜዲካል ላቦራቶሪ ኃ.የተ.የግ.ማ
ARSHO MEDICAL LABORATORIES PLC

በትውልድ የታመነ!

አድራሻ- አራት ኪሎ፣
ከአራዳ ክፍለ ከተማ ሕንፃ ጀርባ፣
የ24 ሰዓት አገልግሎት
612
0114-16-70-89
0911-10-18-18


# መገናኛ ብዙኃን ሚዛናዊ መረጃዎችን በማቅረብ የተዛቡ ትርክቶችና ጥላቻን ማስወገድ እንደሚገባቸው ተጠቆመ

ዳንኤል ዘነበ

ባህር ዳር ፡- መገናኛ ብዙኃን አብሮነትን፣ መከባበርንና መተዋወቅን መሠረት ያደረጉ ትክክለኛና ሚዛናዊ መረጃዎችን በማቅረብ የተዛቡ ትርክቶችና ጥላቻን ማስወገድ እንደሚገባቸው የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ዶክተር ይልቃል ከፋለ ተናገሩ፡፡

የአማራ ሚዲያ ኮርፖሬሽን አሚኮ ኀብር የተሰኘውን ሁለተኛ ቻናሉን ትናንት ባስጀመረበት ወቅት የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ዶክተር ይልቃል ከፋለ እንደተናገሩት ፤ ኢትዮጵያ ብዙ ቋንቋ፣ ሃይማኖት፣ ባሕልና ሥነ ምህዳር የሚገኝባት መልከ ብዙ ናት፣ እኛ ኢትዮጵያውያን ልክ እንደ ነብሩ ዥንጉርጉር በሚል የምንገለጽ ነን ፡፡መገናኛ ብዙኃን አብሮነትን፣ መከባበርንና መተዋወቅን መሠረት ያደረጉ ትክክለኛና

መገናኛ ብዙኃን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ዶክተር ይልቃል ከፋለ




ፎቶ - ፀሐይ ንጉሤ

# የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት ዘላቂ ሠላምና ልማት እንዲጠናከር ቻይና ድጋፍ እንደምታደርግ ገለጸች

አዲሱ ገረመው

አዲስ አበባ፡- የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት ዘላቂ ሰላምና ልማት እንዲጠናከር ቻይና ድጋፍ እንደምታደርግ ገለጸች። የመጀመሪያው የቻይናና አፍሪካ ቀንድ ሀገራት የሰላም፣ የአስተዳደርና የልማት ኮንፈረስ ተካሂዷል።

ሰላምና ልማት ላይ ትኩረቱን ያደረገው የመጀመሪያው የቻይናና አፍሪካ ቀንድ ሀገራት ኮንፈረንስ ትላንት በአዲስ አበባ ከተማ መካሄድ ጀምሯል። በመድረኩም በቻይና ፍላጎት መሠረት የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት ዘላቂ ሰላምና ልማት እንዲጠናከር እየተሠራ እንደሆነ፤ ቻይና ለቀጠናው ሀገራት መጠናከር ሙሉ ትብብር እንደምታደርግ ገልጻለች።

በአፍሪካ ቀንድ የቻይና ልዩ መልዕክተኛ ዡ ቢንግ በመድረኩ እንደገለጹት፤ ቻይና የአፍሪካ ቀንድ ሀገራትን በሰላም፣ በልማትና በአስተዳደር ዘርፍ ለመደገፍ ቁርጠኛ ናት። በቀጠናው ያሉት ሀገራት አንድነት እንዲጠናከር

የአፍሪካ ቀንድ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል







# የቱሪዝም ተጠቃሚነትን ለማሳደግ ለዱር ሕይወት ጥበቃ ተገቢውን ትኩረት መስጠት እንደሚገባ ተገለጸ

**ወርቁ ማሩ**

ሃዋሳ፡- የቱሪዝም ሃብታችንን በአግባቡ ለመጠቀም ለዱር ሕይወት ጥበቃ ሥራ ተገቢው ትኩረት መስጠት እንደሚገባ የዱር እንስሳትና ጥበቃ ባለስልጣን አስታወቀ፡፡

በባለስልጣኑ ለብዙ ዓመታት የሠሩትና የዘርፉ መሪ ተመራማሪ የሆኑት ዶክተር ፋኑኤል ከበደ "ስለኢትዮጵያ" በሚል የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሃዋሳ ባዘጋጀው የፓናል ውይይት ላይ ባቀረቡት የመነሻ ሃሳብ እንደገለፁት፤ የዱር እንስሳት ጥበቃ ሥራ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች ያሉት ሲሆን ለቱሪዝም ያለው አስተዋፅኦ ደግሞ የላቀ ነው፡፡

እንደ አቶ ፋኑኤል ገለፃ፤ የዱር እንስሳትን የምንጠብቃቸው ለመጠቀም ነው፡፡ እኛ ብቻ ሳንሆን ከእኛ ቀጥሎ ያለው ትውልድም እንዲጠቀምባቸውና ትውልድ እንዲቀጥል ጭምር ነው፡፡

አካባቢያችንንም ሆነ የተፈጥሮ ሃብታችንን በአግባቡ ካልጠበቅንና ካልተንከባከብን ትውልድ ሊቀጥል አይችልም ያሉት ዶክተር ፋኑኤል፣ ምክንያቱም ሕይወታችን በሙሉ የተመሠረተው በተፈጥሮ ላይ ነው ብለዋል፡፡

አካባቢያችንን በደምብ ባለመያዛችን የሚደርስብን ጉዳት እጅግ በጣም የከፋ ስለሚሆን ሁሉም ሰው ለተፈጥሮ ሃብት ጥበቃ የበኩሉን አስተዋጽኦ ማድረግ እንዳለበት አስገንዝበዋል፡፡

በሀገራችን የአካባቢ ጥበቃ ሥራ በ15ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በዘርዓ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት እንደተጀመረ የጠቆሙት ዶክተር ፋኑኤል፤ በወቅቱ ከሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ወደ አዲስ አበባ እየመጡ



ፎቶ፡- ዳኜ አበራ

ዶክተር ፋኑኤል ከበደ

አንዳንድ የእጽዋት ዝርያዎችን ያራቡ እንደነበረ ጠቁመዋል፡፡

በመስኪዶች እና በአብያተ ክርስቲያናት ቅጥር ግቢዎች ውስጥ የሚታዩት የጥበቃ ሥርዓቶች ዛሬ ላለው ስነምህዳር ትልቅ አስተዋፅዖ እንዳላቸውም ዶክተር ፋኑኤል ጠቁመዋል፡፡

ኢትዮጵያ ከተፈጥሮ ሀብት አንጻር የታደለች ሀገር መሆኗን ያነሱት ዶክተር ፋኑኤል፤ የአፍሪካ ጣሪያ ከሚባለው የሰሜን ተራራ ከምድር ወለል በታች 110 ሜትር ዝቅታ የሚገኘው ዳሎል ዲፐሬሽን ድረስ ተለያይነት ያላት መሆኗ በውስጡ የስነምህዳር ተለያይነት ይፈጥራል፤ ይህ ደግሞ የሕይወት ተለያይነት እንዲኖረን ያደረገ ነባራዊ ሁኔታ ነው ብለዋል፡፡

በሌላ በኩል አፍሪካ ውስጥ ከሚገኙ ከሶስት ሺህ ሜትር በላይ ከፍታ ካላቸው ቦታዎች 80 ከመቶ የሚሆኑት የሚገኙት ኢትዮጵያ ውስጥ በመሆኑ ለቱሪዝም ሀብት ትልቅ እድል ነው ብለዋል፡፡

በሀገራችን 74 የሚሆኑ የጥበቃ ስፍራዎች መለየታቸውንና ይህ ደግሞ አጠቃላይ የሀገሪቱን 10 ከመቶ እንደሚሸፍንም ዶክተር ፋኑኤል ጠቁመዋል፡፡

ከዚህም ባሻገር ኢትዮጵያ ውስጥ ሁለተኛው ትልቁ የአጥቢ እንስሳት ድንበር ተሻጋሪ ጉዞ ከጋምቤላ ወደ ደቡብ ሱዳን ይካሄዳል ያሉት ዶክተር ፋኑኤል፣ ይህንን ለቱሪዝም ምንጭነት ማዋል ይቻላል ብለዋል፡፡

ከዚህም ባሻገር ኢትዮጵያ በዓለም ላይ በዱር እንስሳት ሀብት ሀብታም ከሚባሉ 25 ሃገሮች አንዷ መሆኗን ጠቁመዋል፡፡

ዶክተር ፋኑኤል እንደገለጹት፣ የዱር እንስሳት ለስነምህዳር ካላቸው ቀጥተኛ ፋይዳ ባሻገር ኢኮኖሚያዊ ፋይዳቸውም የላቀ ነው፡፡ ለአብነትም አንድ ኒያላ 15 ሺህ ዶላር ይሸጣል፤ አንድ ጅብ 180 ዶላር ይሸጣል፤ አንድ ጥንቸል 60 ዶላር ይሸጣል፣ ይህ በራሱ ሃብት ነው ብለዋል፡፡

በሌላ በኩል 80 ከመቶ ጎብኚዎች የዱር እንስሳትን ለመጎብኘት ነው የሚመጡት ያሉት ዶክተር ፋኑኤል፤ ዘርፉ 40 ከመቶ የሥራ እድል እንደሚፈጥርም ጠቁመዋል፡፡ እነዚህን ነገሮች በደምብ ማየት እና የዱር እንስሳት ጠቀሜታው ከፍ ያለ መሆኑን በመገንዘብ መንከባከብ ይገባል ብለዋል፡፡

በመሆኑም ሳቢ የሆነ አካባቢን በመፍጠር ቱሪስት በመሳብና ገቢ በማግኘት እንዲሁም ከራሳቸው ከዱር እንስሳት የሚገኘውን ገቢ በማሳደግ ራሳችንንም ሆነ ሀገራችንን መጥቀም እንደምንችል ዶክተር ፋኑኤል አስገንዝበዋል፡፡



ፎቶ፡- አዮብ ተፈሪ

# «በጦርነቱ ለወደሙ ትምህርት ቤቶች አንድ ሚሊዮን መጽሐፍት ድጋፍ እናደርጋለን»

**- አቶ አክሊሉ ታደሰ**

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- በአፋርና በአማራ ክልል በጦርነቱ ምክንያት ለወደሙ ትምህርት ቤቶች አንድ ሚሊዮን መጽሐፍት ድጋፍ ለማድረግ ዕቅድ ይዘናል ሲሉ በአሜሪካ ላስቬጋስ የሚኖሩት ትውልደ ኢትዮጵያዊው አቶ አክሊሉ ታደሰ ገለጹ። ዲያስፖራው ሀገራችን ያለችበትን ነባራዊ ሁኔታ ባገናዘበ መንገድ ሊንቀሳቀስ እንደሚገባም አመልክተዋል።

በአሜሪካ በላስቬጋስ የሚኖሩት ትውልደ ኢትዮጵያዊው አቶ አክሊሉ ታደሰ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ መልካም መሥራት ለሁሉም የሚበጅ ተግባር ነው። ዲያስፖራው ለሀገሩ በርካታ ድጋፎችን አድርጓል፣አሁንም ድጋፍ እያደረገም ይገኛል። በቅርቡ ከሪቮ ካፕ ፋውንዴሽን መሥራች ከ28 ሺ በላይ መጽሐፍትን ለአብርኆት ቤተ መጽሐፍት አስረክበዋል።

የሪቮካፕ ፋውንዴሽ ከአንድ ሚሊዮን በላይ የትምህርት መጽሐፍትን በጦርነት ለወደሙ ለአፋርና አማራ ክልል ትምህርት ቤቶች ድጋፍ ማድረግ ዕቅድ እንዳለው የገለጹት አቶ አክሊሉ፤ ትልቁ ጫና መጽሐፍትን ማሰባሰብ ሳይሆን ከተሰበሰቡ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ለማጓጓዝ የሚጠይቀው የትራንስፖርት ወጪ ነው። ይህ ደግሞ በአሜሪካ በተለያዩ ግዛቶች ያሉ ኢትዮጵያውያን ከተባበሩ ቀላል ነው ብለዋል።

የሪቮካፕ ፋውንዴሽን መሥራች ከአንድ ሲኒ ቡና 10 ሳንቲም ከአንድ ከተፈጨ ከረጢት አንድ ዶላር እያጠራቀሙ መጽሐፍትን እየገዙ ለሀገራቸው ከ200 ሺ በላይ መጽሐፍት ድጋፍ ማድረጋቸውን ያስታወሱት አቶ አክሊሉ፤ ዲያስፖራው በቀን ሁለት ስኒ ቡና የሚጠጣ ከሆነ የአንዱን ስኒ ቡና ለድጋፍ ቢያውለው ከባድ የሆነውን ችግር ማቅለል እንደሚቻል ገልጸዋል።

እንደ አቶ አክሊሉ ገለጻ፤ዲያስፖራው መንግሥትን በመቃወም ብቻ መጠመድ ሳይሆን በችግር ላይ ላሉ ለዜጎቻችንም መደገፍ አለበት። መቃወም ባለብን ጊዜ መቃወም ችግር የለውም ነገር ግን ሀገርን አሳልፎ በሚሰጥ መልኩ መሆን የለበትም። መጽሐፍት የሚመጣው ትምህርት ለሚማሩ ዜጎች እንጂ ለፖለቲከኞች ባለመሆኑ ለድጋፉ መተባበር ያስፈልጋል።

ዜጎችን እየደገፉ የሚስተካከሉ ነገሮችን ደግሞ እንዲስተካከሉ ማድረግ የሰለጠነ የፖለቲካ አካሄድ መሆኑን ነው የተናገሩት አቶ አክሊሉ።

ባለፉት 40 ዓመታት የተለመደው ተግባር ከመንግሥት ጋር ተጣልቶ በመሄድ ሚስጥርን ለሌሎች አገራት አሳልፎ መስጠት መሆኑን አውስተው፤ እነዚህ ውስን የምዕራባውያን አገራት እኛው በሰጠናቸው መረጃ ሊያፈርሱን ይፈልጋሉ።ከዚህ አኳያ ዲያስፖራው ይህን በመገንዘብ ለአገሩ ዘብ መቆም አለበት ብለዋል።

ሀገራችን ያለችበትን ነባራዊ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ ዲያስፖራው መንቀሳቀስ እንዳለበት የገለጹት ትወልደ ኢትዮጵያዊው፤ አገር ከምንም በላይ ይቀድማል፡፡ በሀገራዊ የኃላፊነት ስሜት መንቀሳቀስ ያስፈልጋል። በፖለቲከኛ ምክንያት አገር አትሰደብም፤ አትጠላም ነው ያሉት።

በአፋርና በአማራ ክልል በጦርነቱ ምክንያት የወደሙ ትምህርት ቤቶችን መልሶ ለመገንባት ትምህርት ሚኒስቴር ባወጣው ዕቅድ መሠረትም የትምህርት መጽሐፍት ድጋፍ ለማድረግ ዝግጁ ነን ያሉት አቶ አክሊሉ ፤የሪቮካፕ ፋውንዴሽን መሥራች ከአንድ ሚሊዮን በላይ መጽሐፍት ድጋፍ ለማድረግ ቃል መግባቱንም አስታውቀዋል።

ዲያስፖራውም ሆነ አገር ውስጥ ያሉ ባለሃብቶች ከውጭ የሚገቡ መጽሐፍትን የትራንስፖርት ወጪ ድጋፍ በማድረግ አገራዊ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡም ጥሪ አቅርበዋል።

# ባለሥልጣኑ በሕገ ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ዝውውር ላይ የሚያደርገውን ቁጥጥር አጠናክሮ መቀጠሉ ተገለጸ

**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡- በሕገ ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ዝውውር ላይ የሚያደርገውን ቁጥጥር አጠናክሮ መቀጠሉን የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን ገለጸ፡፡

የባለስልጣኑ የቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ማስተባበሪያ ዳሬክቶሬት ዳይሬክተር ዶክተር ገመዳ ቢነግዴ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ሕገ ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ማምረት፣ማዘዋወር እንዲሁም ማከፋፈል እና ንግድ ላይ የሚደረገው ቁጥጥር ተጠናክሮ ቀጥሏል፡፡ለተጠናከረ የቁጥጥር ሥራ እንዲያመች ሕገ ወጥ ዝውውር በብዛት የሚንቀሳቀስባቸውን አካባቢዎች በጥናት በመለየት ወደ ሥራ ተገብቷል፡፡

እንደ ሀገር ባለስልጣኑ በሁሉም ቦታ ተደራሽ ሆኖ ለመቆጣጠር ምቹ ሁኔታዎች ባይኖሩም በጥናት በተለዩት አካባቢዎች ሥራዎች በስፋት እየተከናወኑ መሆኑን ጠቁመው፤ የሕዝብ ንቅናቄዎችን በማድረግ፣ ከክልሎች ጋር ቅንጅታዊ ሥራዎችን በማጠናከር ፣በዘርፉ ለተሰማሩ ባለሙያዎች የእንስሳት መድኃኒት አያያዝ እና አጠቃቀም ሥርዓት ስልጠና በመስጠት ክትትል እንደሚያደርግ ጠቅሰዋል፡፡

ሕገ ወጥ እና ደህንነታቸው ያልተረጋገጠ የእንስሳት መድኃኒቶች በእንስሳቱ እና በኅብረተሰቡ ጤንነት ላይ ጉዳት ከማድረሱም በላይ ምርትና ምርታማነትን በመቀነስ በሀገር ኢኮኖሚ ላይ ትልቅ ተጽዕኖ እንደሚያሳድሩ የገለጹት ዳይሬክተሩ፤ ባለስልጣን መሥሪያ ቤቱ ሕገ ወጥ የእንስሳት መድኃኒቶቹ ተሰራጭተው ጉዳት እንዳያደርሱ ከፍተኛ ክትትል እና ቁጥጥር እንደሚያደርግ ተናግረዋል፡፡እርምጃዎች የሚወሰዱትም በቂ ግንዛቤ ከተሰጠ በኋላ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

ባለስልጣን መሥሪያ ቤቱ የሚቆጣጠረው ድንበር ተሻግረው የሚገቡና የሚወጡ እንዲሁም ክልል ተሻጋሪ ሕገ ወጥ የእንስሳት መድኃኒቶች ላይ መሆኑን ገልጸው፤ መድኃኒቶቹ ጥራታቸው፣ደህንነታቸው እና ፈዋሽነታቸው ላይ ትኩረት እንደሚደረግ አብራርተዋል፡፡

ክልሎች የቁጥጥሩን ሥራ በራሳቸው እንደሚያከናውኑ ገልጸው በስድስት ቅርንጫፎች እና በስምንት የመግቢያና መውጫ ክልሎች አማካኝነት በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች የቁጥጥሩን ሥራ ወደ ተሻለ ደረጃ ለማድረስ እየተሠራ እና አበረታች ውጤት እየተገኘ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ቁጥጥሩ የሚደረገው በሕገ ወጥ ብቻ የሚገቡትን ሳይሆን በሕጋዊ ሽፋን ፍቃድ አውጥተው ሕገ ወጥ ሥራ ላይ የሚሰማሩትንም እንደሚጨምርም ገልጸዋል፡፡

ዶክተር ገመዳ ቢነግዴ እንደሚሉት በአምራቾች፣ በጅምላ አከፋፋዮች እንዲሁም በችርቻሮ መደብሮች ላይ ከክልሎች ጋር በቅንጅት ቁጥጥር ይደረጋል፡፡ሕጋዊ ሥርዓትን ሳይከተሉ በሕገ ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ንግድና ስርጭት ሥራ ላይ ተሰማርተው በሚገኙት ሕገወጦች ላይ እርምጃ እየተወሰደ ይገኛል፡፡ ቅጣቱም የብቃት ማረጋገጫ ፍቃድ እስከማገድ እንዲሁም ክስ መስርቶ በወንጀል እስከማስጠየቅ ይደርሳል፡፡

በሕገወጥ መንገድ ወደ ሀገር ውስጥ ሲገቡ የተያዙ በርካታ ሕገ ወጥ የእንስሳት መድኃኒቶች ወደ መጡበት



ዶክተር ገመዳ ቢነግዴ

እንዲመለሱ እና እንዲወገዱ የተደረጉ እንዳሉም ጠቁመዋል፡፡

ከመድኃኒት እና ምግብ አስተዳደር እና ቁጥጥር ባለስልጣን፣ከጉምሩክ እና ከፍትሕ አካላት ጋር በመቀናጀት ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን ጠቁመው፤ ቀሪ ሥራዎች ቢኖሩም እየተደረገ ባለው የቁጥጥር ሥራ ለውጦች እየመጡ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ የቁጥጥሩ ሥራም የሁሉንም ድጋፍ ስለሚፈልግ ሁሉም ማኅበረሰብ ከባለስልጣኑ ጎን በመሆን ድጋፍ እንዲያደርግ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

# “የሕግ የበላይነትን የማስፈን ሥራ በሽብር ቡድኖች ሴራ አይደናቀፍም”

-የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ:- መንግሥት የጀመረው የሕግ የበላይነትን የማስፈን ስራ በሽብር ቡድኖች ሴራ እንደማይደናቀፍ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ገለጸ፡፡

አገልግሎቱ በማኅበራዊ ትስስር ገጹ ላይ ባሰፈረው መልዕክት እንደገለጸው፤ መንግሥት በመላ ሀገሪቱ ሰላምን ለማስፈን የኢ-መደበኛ ታጣቂዎችንና በሽብር ቡድንነት የተፈረጁ ቡድኖችን እንቅስቃሴ ለመግታት ሁሉን አቀፍ ጥረት እያደረገ ይገኛል።

ይህ የመንግሥትና የመላው ጸጥታ ኃይላችን የሕግ የበላይነትን የማስከበር ተልዕኮ ያነጣጠረበት የሸኔ የሽብር ቡድን እየደረሰበት የሚገኘውን ከፍተኛ ሽንፈት ለመሸፈን የጥፋት በትሩን ወደ ንጹሓን አዙሯል ብሏል።

የሽብር ቡድኑ በቅርቡ በጋምቤላ፣ በደምቢዶሎና በጊምቢ ከተሞች ላይ የሰነዘራቸው የሽብር ጥቃቶች በጸጥታ ኃይሉ ቅንጅት ሲከሸፍ በበቀል የሽብር ተግባሩ በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ወለጋ ዞን ጊምቢ ወረዳ ውስጥ ነዋሪ የሆኑ በርካታ ንጹሓንን ሕይወት በግፍ ቀጥፏል፣ ንብረትንም አውድሟል ብለዋል።

አገልግሎቱ በሽብር ጥቃቱ ሕይወታቸውን ላጡ ወገኖችና ለደረሰው ጉዳት መንግሥት የተሰማውን ልባዊ ኀዘን ይገልጻል ብሏል ፡፡

ይህ ቡድን በንጹሓን ላይ የሚያደርሰው ጉዳት የቡድኑን ትክክለኛ ማንነት የሚያሳይ በመሆኑ የጥፋት ኃይሉ ሙሉ በሙሉ እንዲደመሰስ በመላው የክልልና የፌደራል የጸጥታ ኃይሎች የተጀመረው የተቀናጀ ተልእኮ ተጠናክሮ ይቀጥላል ሲልም መልዕክት አስተላልፏል።




# አገልግሎቱ የሀገር ውስጥ መድኃኒት አቅራቢዎችና አምራቾችን አቅም ለማሳደግ እየሠራ መሆኑን ገለጸ

ውብሸት ሰንደቁ

አዲስ አበባ:- በማሽቆልቆል ላይ የሚገኘውን የሀገር ውስጥ መድኃኒት አቅራቢዎችና አምራቾች አቅም ለማነቃቃትና ለማሳደግ እየሠራ መሆኑን የኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ አገልግሎት አስታወቀ፡፡

የኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ አገልግሎት ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ሰለሞን ንጉሴ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ በሀገሪቱ መድኃኒት አቅራቢዎች እና አምራቾች በግብዓት አቅርቦት፣ በውጪ ምንዛሪ እጥረት እና በአሠራር ክፍተቶች እየተፈተኑ ቆይተዋል፡፡

ከሦስት ዓመት በፊት የሀገር ውስጥ አቅራቢዎች ሽፋን 25 በመቶ እንደነበር የጠቀሱት አቶ ሰለሞን፤ በአሁኑ ወቅት ግን ሽፋናቸው ወደ 10 በመቶ ማሽቆልቆሉን ጠቁመዋል፡ ፡ ለዚህም የዘርፉን ተዋናዮች ያካተተ ሀገር አቀፍ ግብረ ኃይል ተቋቁሞ እየሠራ ነው ብለዋል፡፡

የኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ ኤጀንሲ የሀገር ውስጥ አቅራቢዎችን ድርሻ ወደ 60 በመቶ ከፍ ለማድረግ አቅዶ ሲሠራ ቢቆይም ዕቅዱ በተለያዩ ችግሮች ምክንያት ሳይሳካ ቆይቷል ብለዋል፡፡

እንደ አቶ ሰለሞን ገለፃ፤ በመድኃኒት አቅራቢዎች ላይ ያለው ችግር እንዳይባባስ የኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ አገልግሎት በተለያየ መንገድ ድጋፍ ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ ለአብነትም 30 በመቶ ቅድሚያ ክፍያ መክፈልን ጨምሮ ዘርፉ እንዳይቀጭጭ በማሰብም መጀመሪያ የሀገር ውስጥ



አቶ ሰለሞን ንጉሴ

ጨረታ ብቻ በማውጣት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ሲደረጉ ቆይተዋል፡፡ የውጪ ጨረታ በሚወጣበት ጊዜም የሀገር ውስጥ አምራቾችና አቅራቢዎች እንዲሳተፉ በማድረግ እና በዋጋ ደረጃ የሀገር ውስጥ አቅራቢ ተቀራራቢ ብልጫ ሲኖረው ለሀገር ውስጡ ቅድሚያ በመስጠት ድጋፎች ሲሰጡ ቆይተዋል፡፡

ሆኖም ችግሩን ከሥሩ ለመፍታት የተለያዩ አካላትን ቅንጅታዊ አሠራር የሚጠይቅ እንዲሁም የአሠራር መመሪያዎችን ማስተካከል የሚሻ በመሆኑ በሀገር አቀፍ ደረጃ የተቋቋመው ግብረ ኃይል ከተለያዩ አካላት ጋር ሥራዎችን በመሥራት የተመዘገቡ ለውጦች መኖራቸውን ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ አብራርተዋል፡፡

በዚህም በውጭ ምንዛሪ አቅርቦት ላይ እና በትራንስፖርት ረገድ እንዲሁም በታክስ ላይ ለዘርፉ ሳንካ የነበሩ ችግሮች የሀገሪቱ አቅም በፈቀደ መጠን እልባት ተበጅቶላቸዋል ብለዋል፡፡

ከብሔራዊ ባንክ ጋር በመምከር እና የአሠራር ማሻሻያ በማድረግ የሀገሪቱ አቅም በሚፈቅደው መሠረት የግልም ሆነ የመንግሥት ባንኮች የውጪ ምንዛሪ አቅርቦት ቅድሚያ ለመድኃኒት የሚለውን መመሪያ እየተገበሩ መሆኑን በማሳያነት አንስተዋል፡፡

በትራንስፖርት ረገድም ይታዩ የነበሩ ክፍተቶችን ለመቅረፍ በተደረገ ጥረት የመድኃኒት ግብዓቶች ከውጭ ሀገር በአውሮፕላን አልያም በመርከብ ተጓጉዘው ወደብ ላይ በሚደርሱበት ጊዜ ከሌሎች ሸቀጦች በተለየ ሁኔታ ቅድሚያ ተሰጥተው እንዲስተናገዱ እየተደረገ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

ከውጭ የሚገቡ የመድኃኒት ግብዓቶች ልክ እንደ ሌሎች ሸቀጦች ታክስ ይጣልባቸው እንደነበር የገለፁት አቶ ሰለሞን፤ አሁን በተደረገው ማሻሻያ ከታክስ ነፃ እንዲገቡ መደረጉን ጠቅሰው ይህም ዘርፉን እንደሚያነቃቃው ተናግረዋል፡፡

ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ለዘርፉ መነቃቃት ሌሎች ተስፋዎች እንዳሉም አብራርተዋል፡፡ የሀገር ውስጥ ምርትን ለማሳደግ በተሰጠው ትኩረት የፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪ ፓርክ ግምባታው ተጠናቆ የሀገር ውስጥና የውጪ ባለሀብቶች በጆይንት ቬንቸር ሥራ እየጀመሩ መሆኑን ለዘርፉ መነቃቃት ተስፋ እንደሆነ አንስተዋል፡፡



አቶ የሺዋስ አለሙ

# የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልልን ለማጠናከር የገቢ ማሰባሰቢያ መርሐ-ግብር ሊካሄድ ነው

መዓዛ ማሞ

አዲስ አበባ፡ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልልን ለማጠናከር በአዲስ አበባ ሰኔ 15 የመጀመሪያው የገቢ ማሰባሰቢያ መርሐ-ግብር እንደሚካሄድ ተገለጸ።

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች የመንግሥት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ ኃላፊ አቶ የሺዋስ አለሙ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት የገቢ ማሰባሰቢያው "የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልልን ይደግፉ ወንድማማችነትን ያጠናክሩ " በሚል መሪ ቃል ረቡዕ ሰኔ 15 በአዲስ አበባ ሸራተን አዲስ ሆቴል ከምሽቱ 12 ሰዓት ጀምሮ ይካሄዳል።

የገቢ ማሰባሰቢያው ከተመሠረተ የወራት ጊዜ ብቻ ያስቆጠረው የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል አሁን ባለበት ሁኔታ ከፍተኛ የሆነ የበጀት ጉድለት ያለበት በመሆኑ ከሌሎች ወንድም እና እህት ኢትዮጵያውያን ጋር በመሆን ክልሉን ማጠናከር እና ማደራጀት አስፈላጊ በመሆኑ ክልሉን ለማገዝ ያለመ ነው።

ክልሉ ከፍተኛ የሆነ የግብርና ምርቶች፣ የቡና እና የቅመማቅመም እንዲሁም የማዕድናት ሀብት ያሉት እና በቱሪዝሙም ዘርፍ ግንባታው እየተከናወነ ያለው የኮይሻ ፕሮጀክትን ጨምሮ ትልልቅ ፓርኮች እንዳሉበት የተናገሩት የቢሮ ኃላፊው የተዘጋጀው የገቢ ማሰባሰቢያ መርሐ-ግብር እነዚህን በክልሉ ያሉ የቱሪዝም እና የኢንቨስትመንት አማራጮችን ማስተዋወቅ ሌላኛው ዓላማ እንደሆነም ተናግረዋል።

በመጀመሪያው ዙር የገቢ ማሰባሰቢያ መርሐ-ግብሩ የፌዴራል ተቋማት፣ሁሉም ክልሎች፣ ኤምባሲዎች፣ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች እና በኢንቨስትመንት ዘርፍ የተሠማሩ ትልልቅ ባለሀብቶች እንደሚሳተፉ ጠቁመው ሁለተኛ ዙር በክልል ደረጃ በሰኔ ወር መጨረሻ ላይ እንደሚደረግ ገልጸዋል።

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል የሁሉም ኢትዮጵያውያን ክልል ነው ያሉት የቢሮ ኃላፊው አሁን ላይ የገጠመውን ችግር ተባብረን ከፈታን ክልሉ በርካታ የሆኑ ሀብቶች ያሉት በመሆኑ የክልሉ ሀብት ከጥቂት ጊዜ በኋላ ለሁሉም የሚበቃና በተለያየ መንገድ በሂደት የሚመልስ እንደሆነ ገልጸዋል። ክልሉ ሰፊ የሆነ የኢንቨስትመንት አማራጭ ያለው በመሆኑ ባለሀብቶች ወደ ክልሉ በመምጣት ኢንቨስት እንዲያደርጉም ጥሪ አስተላልፈዋል።

# “የውጭ ሀገራት ባንኮች ወደ ሀገር ውስጥ ሲገቡ የሚተገበር የአሠራር ሥርዓት እየተዘጋጀ ነው”

- የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ

ከጋዜጣ ሪፖርተር

አዲስ አበባ፤ የውጭ ሀገራት ባንኮች ወደ ሀገር ውስጥ ሲገቡ የሚተገበር የአሠራር ሥርዓት እየተዘጋጀ መሆኑን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ አስታወቀ።

በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የባንክ ቁጥጥር ዳይሬክተር ፍሬዘር አያሌው የኢትዮጵያን የባንክ ኢንዱስትሪ ለውጭ ሀገራት ክፍት ለማድረግ የፖሊሲ ማሻሻያ በማድረግ ወደ ሥራ ለመግባት በሂደት ላይ መሆኑን ጠቁመው፥ ዘርፉ ብቁና ተወዳዳሪ እንዲሆን በተወሰኑ ተዋናዮች ብቻ ታጥሮ የቆየው የባንክ ኢንዱስትሪ ለውጭ ባንኮች ክፍት የማድረግ እንቅስቃሴ ተጀምሯል ብለዋል።

በዚህም መሠረት ባንኮቹ ወደ ሀገር ውስጥ ሲገቡ ዘርፉ የሚመራበት የአሠራር ሥርዓት እየተዘጋጀ መሆኑን ገልጸው፥ የባንኮች ወደ ሀገር ውስጥ መግባትም ለእውቀትና የቴክኖሎጂ ሽግግር፣ የውጭ ምንዛሪ ፍሰትን ለመጨመር፣ የብድር አገልግሎትን ለማስፋትና ሌሎችም ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች እንዳሉት አብራርተዋል፡፡

በአጠቃላይ በኢትዮጵያ የሚደረገውን የምጣኔ ሃብት እንቅስቃሴ በፋይናንስ መደገፍና አዳዲስ አሠራሮችን ያመጣሉ ተብሎም ይጠበቃል ነው ያሉት፡፡

የባንኮቹ ወደ ሀገር ውስጥ መግባት ከሚኖረው ጠቀሜታ ባለፈ በሂደቱ ሊያስከትል የሚችለውን ስጋት



አቶ ፍሬዘር አያሌው

ሊቀንስ የሚችል የሕግ ማዕቀፍና የአሠራር ሥርዓት እየተዘጋጀ ነው ማለታቸውን ኢዜአ ዘግቧል፡፡

የሀገር ውስጥ ባንኮች ይህንን ታሳቢ በማድረግ በሰው ኃይል፣ በአቅም እና በቴክኖሎጂ ጭምር በመጎልበት ለውድድር ዝግጁ እንዲሆኑ ያስገነዘቡት ዳይሬክተሩ፥ የተጠናከረና የተደራጀ ባንክ ከመፍጠር አንጻር በራሳቸው ፈቃድ አንዱ ከሌላው ጋር የመዋሃድ አማራጭን መከተልም ወሳኝ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክም የሕግ ማዕቀፉ በሚፈልገው ልክ ጠንካራ፣ ብቁና አስፈላጊውን መስፈርት የማያሟሉ ባንኮች ካጋጠሙ በመዋሃድ መሥራት በአማራጭነት የሚወሰድ ስለመሆኑም ጠቁመዋል።



ፎቶ፡- አዲስ አበርሃ

# የፍትሕ ተቋማት የተገልጋዩን ፍላጎት ማሟላት እንዳልቻሉ ጥናት አመለከተ

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- የፌዴራል የፍትሕ ተቋማት የተገልጋዩን ፍላጎት ማሟላት አለመቻላቸውን በዘርፉ የተካሄደ የዳሰሳ ጥናት አመለከተ።ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ ጠቅላይ አቃቤ ሕግ፣ ማረሚያ ቤቶችና ፖሊስ ኮሚሽን ላይ የተካሄደው ሀገር አቀፍ የዳሰሳ ጥናት በትናንትናው ዕለት ይፋ ተደርጓል።

ጥናቱን አስመልክቶ የፍትሕና የሕግ ኢንስቲትዩት የጥናትና ምርምር ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ምትኩ ማዳ እንደገለጹት፤ እንደ ሀገር ለውጥ ከመጣ ጀምሮ በፍትህ ተቋማት ላይ የተወሰነ መሻሻል ቢኖርም በጥራት፣ በሀቀኝነት፣ ሕገ መንግሥቱን መሠረት አድርጎ ከመሥራት አኳያ ክፍተት አለ።

ኅብረተሰቡ ከደረሰበት የፍላጎትና የእርካታ ፍላጎት ደረጃ አንጻር የኅብረተሰቡ አገልግሎት አሁንም በሚፈልገው ደረጃ ላይ አልደረሰም ያሉት ምክትል ዳይሬክተሩ፤ የመልካም አስተዳደርና የአገልግሎት አሰጣጡን በሚመለከት በውስጥ ሠራተኞችና በተገልጋዩ ኅብረተሰብ ሲታይ የኅብረተሰቡ ፍላጎት እየጨመረ የሄደ በመሆኑ አመርቂ አይደለም ብለዋል።

በተለይ በፍትሕ ተቋማት ላይ የሚገለገሉ የውጭ ተገልጋዮች እርካታ በቂ አለመሆኑን ጥናቱ ያሳያል ብለዋል፡፡

እንደ አቶ ምትኩ ገለጻ፤ የፍትሕ ተቋማት ተገልጋዩን ኅብረተሰብ በቅንነት ከማገልገል አንጻር፣ የፍትሕ አካላት በሚፈለገው ልክ ከሙስና የጸዱ አለመሆን፣ የአቅም ማነስ፣ በሕገ መንግስቱ መሠረት እርምጃ አለመውሰድና፣ ጠንካራ የቁጥጥርና ክትትል አለመኖር በተገልጋዩ ዘንድ ችግር እየፈጠረ ነው።

በዚህ የተነሳ አገልግሎት ፈላጊው ኅብረተሰብ እየተንገላታ መሆኑን አቶ ምትኩ ገልጸዋል፡፡

በቀጣይም የተገልጋዩን ኅብረተሰብ ፍላጎት ለማርካት የተገኙ ውጤቶችን መሠረት በማድረግ ዝርዝር መፍትሔዎች ቀርበዋል ያሉት አቶ ምትኩ፤ ስለመጣው ለውጥ የግንዛቤ ችግር ስላለ በፍትሕ ተቋማት ውስጥ የሚሠሩ የውስጥ ሠራተኞች በሚፈለገው ልክ የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ መሥራት ይጠይቃል ብለዋል።

እንደ አቶ ምትኩ ገለጻ፤ የጥናት ግኙቱ እንዳመላከተው በሁሉም የፍትሕ ተቋም የስነምግባር ችግር ያለ በመሆኑ ሁሉም ተቋማት የኅብረተሰቡን እርካታ ሊያረጋግጡ በሚችሉበት ሁኔታ መሥራት አለባቸው።አገልግሎት አሰጣጡ የየተቋሙን አገልግሎት ሊመጥን በሚችል ሁኔታ ሊሆን ይገባልም ብለዋል፡፡

ጥፋት የሚያጠፉ የፍትሕ ተቋማት ላይ አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ ይገባል ያሉት አቶ ምትኩ፤ የፍትሕ ተቋማት በዕለት ተዕለት በርካታ ተገልጋዮች የሚመጡባቸው በመሆኑ እየታዩ ያሉ ችግሮችን በፍጥነትና በትኩረት ማስተካከል አስፈላጊ ነው ብለዋል።

# መገናኛ ብዙኃን ሚዛናዊ...

ከገፅ 1 የዞረ

ሚዛናዊ መረጃዎችን በማቅረብ የተዛባ ትርክትንና ጥላቻን ማስወገድ ይገባል፡፡

በሐሰት ትርክት ላይ ተጠምዶ፣ በጽንፈኝነት ጫፍ ተንጠላጥሎ፣ሕዝብን በጥላቻ መነጽር እያየ፣ አንዱን ከአንዱ እያጋጨ መኖር እንደ ልምድና እንደ ጀግንነት መቆጠር እየተለመደ መጥቷል ያሉት ርዕሰ መስተዳድሩ፤ይህም እርስ በእርሳችን ለመተዋወቅ ባለመዘጋጀታችን ፣ ሚዛናዊና እውነተኛ መረጃ በየአካባቢው መድረስ ባለመቻሉ ልዩነቶችን እንደ ስጋት በመቁጠር በርካታ ግጭቶች ተፈጥረዋል ፡፡ በግጭቱ ተጠቂ የነበረው የአማራው ሕዝብ ነው ብለዋል ፡፡

የአማራ ሕዝብ በጎረቤት ሀገራት ጨምሮ በእውነተኛ መረጃ ላይ የተመሠረተ ስም የለውም ያሉት ርዕሰ መስተዳድሩ፤መገናኛ ብዙሃን የተዛባውን ትርክት በማስረዳት ለሚጠሉንና ለሚወነጅሉን ትክክለኛ መረጃ በመስጠት ራስን የማስተዋወቅ ኃላፊነት አለባቸው ሲሉ አስገንዝበዋል ፡፡

እንደ ሀገር ብቻ ሳይሆን የምሥራቅ አፍሪካ ሕዝቦች ዕጣ ፋንታ በአንድነት የተጋመደ መሆኑን ያነሱት ርዕሰ መስተዳድሩ ፤ በዚህ ረገድ መገናኛ ብዙኃን አብሮነትን፣ መከባበርንና መተዋወቅን መሠረት ያደረጉ ትክክለኛና ሚዛናዊ መረጃዎችን በማቅረ የተዛባ ትርክትንና ጥላቻን ማስወገድ እንደሚገባም አስገንዝበዋል ፡፡

አሚኮ ኅብር የአማራ ክልል ብዝኃ ልሳንን ከማጠናከር አልፎ ኢትዮጵያውያን በሙሉ እንዲተዋወቁ እና ያለንን ኃብት በፍትሐዊነት ተጠቅመን እንድንኖር መንገድ ይከፍታል ብለዋል ፡፡

ሁላችንንም ልዩነታችንን እርስ በእርስ ተዋውቀን፣ ተከባብረን እና ተደማምጠን ከያዝናቸው የግጭት ምንጭ ሳይሆኑ የጌጥና የውበት ምንጭ ሆነው የሚያገለግሉ እንደሆነ ገልጸዋል ።

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የመንግሥት ኮሙዩኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ዶክተር ለገሰ ቱሉ በበኩላቸው ፤ አሁን ላይ ሚዲያዎች ላልተፈለገ ጽንፈኝነት እና አክራሪነት ተጋልጠዋል። ሚዲያዎቹ የኅብረተሰቡን ፍላጎት በትክክል መግለጽ ያልቻሉበት ጊዜ ላይ መድረሱን ገልጸዋል ፡፡

አብዛኞቹ ሚዲያዎች ኅብረተሰብን ከማቀራረብ ይልቅ የሚያራርቁ ኅብረተሰብን አንድ ከማድረግ ይልቅ የሚበትኑ አስተሳሰቦችን በማራገብ የአድኃሪያን አስተሳሰብ እንደተጠናወታቸውም አስረድተዋል ፡፡

በዚህ ሂደት አሚኮ የሕዝብ ልሳን በመኾን የሕዝብን ፍላጎት እና ትክክለኛ አመለካከት በማውጣት አኩሪ ሥራ ሲሠራ መቆየቱን አስታውሰው ፤ አሚኮ ለውጡ በአማራ ክልል እንዲቀጣጠል በማድረግ አኩሪ ታሪክ የፈጸመና ለውጡ ፈር እንዲይዝ እና ሕዝቡ ለውጡን ጠብቆ እንዲዘልቅ በማድረግ የሠራው ሥራ የሚያኮራ መሆኑን አውስተዋል ፡፡

በሌላ በኩል መንግሥት ሕግ በማስከበር በኩል ለሚሠራው ሥራ ትክክለኛ መረጃ በማቀበል እየሠራ በመሆኑ መንግሥት ከፍተኛ ምሥጋና አለው ብለዋል ፡፡

"አሚኮ አዲሲቷን ኅብረ ብሔራዊት ኢትዮጵያ ለመገንባት በሚደረገው ጥረት የድርሻውን እየተወጣ ያለ ሚዲያ ነው " ያሉት ደግሞ የአማራ ሚዲያ ኮርፖሬሽን ቦርድ ሰብሳቢው አቶ ግርማ የሺጥላ ፤ የተሳሳተ ትርክትን በማረም የክልሉን ሕዝብ እውነተኛ ማንነት ለዓለም እንደሚገልጥም አመልክተዋል፡፡

የቦርድ ሰብሳቢው ኮርፖሬሽኑ ዓለም የደረሰበትን የሚዲያ ቴክኖሎጂ እንዲታጠቅ እና ብቁ ባለሙያዎችን እንዲያፈራ የክልሉ መንግሥት በትኩረት እየሠራ መኾኑንም አስታውቀዋል፡፡ የፌዴራል መንግሥት እና አጋር አካላት ከኮርፖሬሽኑ ጋር በጋራ እንዲሠሩም ጥሪ አቅርበዋል፡፡

# ጥቃት በደረሰባቸው አካባቢዎች...

ከገፅ 1 የዞረ

ዘግናኝ ድርጊት የምንታገሰው አይደለም" ብለዋል።

በተያያዘ ዜና የኢፌዲሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን በማኅበራዊ ትስስር ገጻቸው ባስተላለፉት መልዕክት እንደገለጹት፤ በፀጥታ አስከባሪ አካላትና በሕዝቡ የተባበረ እርምጃ በደረሰበት ሽንፈትና ኪሳራ አሸባሪውና ፅንፈኛው ቡድን የቀቢፀ ተስፋ እርምጃዎችን እየወሰደ ይገኛል፡፡

በቅርብ ጊዜ በጋምቤላ አካባቢ ያደረገው ሙከራ ሲከሽፍበት በምዕራብ ወለጋ በጊምቢ አካባቢ ደግሞ በንፁሓን ዜጎች ላይ በተለይም በሕጻናትና በሴቶች ላይ ያካሄደው ጭፍጨፋ እጅግ አሳዛኝ እና ኢ-ሰብዓዊ ነው ብለዋል፡፡

አቶ ደመቀ በተለያዩ አካባቢዎች ቡድኑ በወሰደው እኩይ የጥፋት እርምጃ ምክንያት በንፁሓን ወገኖቻችን ላይ ለደረሰው ጉዳት የተሰማኝን ጥልቅ ኀዘን እየገለጽኩ፤ በመንግሥት በኩል ሕግ የማስከበር እርምጃው ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ላረጋግጥ እወዳለሁ ብለዋል።

በቀጣይ ተጎጂ ቤተሰቦችን የማረጋጋት፣ የመደገፍ እና መልሶ የማቋቋም ሥራ በትኩረት የሚሠራ ሲሆን፤ አሸባሪዎችን እና ጽንፈኞችን ለሕግ የማቅረቡ ሥራ ተጠናክሮ እንደሚቀጥልም ገልጸዋል።

የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ዶክተር ይልቃል ከፋለ በኦሮሚያ ክልል በምዕራብ ወለጋ ዞን ግምቢ ወረዳ ቶሌ ቀበሌ አሸባሪው ሸኔ በንጹሐን ወገኖች ላይ በፈጸመው ግድያ የተሰማቸውን ኀዘን ገልጸው፤የጉዳቱ ሰለባ ለሆኑ ቤተሰቦቻቸውም መጽናናትን እመኛለሁ" ብለዋል።

"ድርጊቱ ሀገራችንን ከአሸባሪዎች ለማጽዳት የጀመርነውን ዘመቻ አጠናክረን ከመቀጠል ውጪ ሌላ አማራጭ እንደሌለን ማሳያ ነው" ሲሉም ርዕሰ መስተዳድሩ አስታውቀዋል።

# የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት ዘላቂ...

ከገፅ 1 የዞረ

ከሀ ገራቱ ጋር በጋራ ለመሥራት ከፍተኛ ፍላጎት አላት።

የአፍሪካ ቀንድ በሁሉም መስክ ትልቅ አቅም ያለው ሥፍራ እንደሆነ የጠቀሱት ልዩ መልዕክተኛው፤ ከጊዜ ወደ ጊዜ በሠላምና ደህንነት እንዲሁም በኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ቀጣናው እየተፈነ መሆኑን ጠቁመዋል። የአካባቢውን ሕዝብ ሰላም ማስጠበቅና በዘላቂ ኢኮኖሚ ማበልጸግ እንደሚገባም ገልጸዋል። ለዚህ ደግሞ ቻይና ድጋፍ ለማድረግ ዝግጁ እንደሆነች አስታውቀዋል።

ቻይና የቀንዱ ሀገራት ወዳጅ እንደመሆኗ፤ በተለይም በጸጥታው ዘርፍ፣ በሰደት፣ በድርቅና መሰል የቀጠናው ሀገራት ተግዳሮቶች የሆኑ ጉዳዮች ላይ መፍትሔ ሊሠጡ የሚችሉ ድጋፎችን እንደምታደርግ ነው ልዩ መልዕክተኛው የተናገሩት። ይህ ደግሞ የወደፊት የቻይና-አፍሪካ ማኅበረሰብን ለመጠናከር መነሳሳትን ይፈጥራል ብለዋል።

የጠቅላይ ሚኒስትሩ የብሔራዊ ደህንነት አማካሪ አምባሳደር ሬድዋን ሁሴን፤የአፍሪካ ቀንድ በቁጥር በርካታ አምራች ዜጎች ያለው ቢሆንም፤ በሰው ሠራሽና ተፈጥሮአዊ አደጋዎች ሲታመስ መቆየቱን ገልጸዋል። ኮንፈረንሱ የቀጠናው ሀገራት በአንድነት ተቀምጠው ችግሮቻቸውን እንዲፈቱ ያስችላል በማለት፤ በተለይም የቻይና መንግሥት በልማትና ሰላም ጉዳይ ለቀንዱ ሀገራት እያደረገ ያለውን ትብብር አድንቀዋል።

ቀጠናው አቅሙን በመጠቀም፣ ሰላምና ጸጥታውን በማሻሻል፣ እንዲሁም የታሪክና የባህል እሴቱን በማጠናከር በጋራ መለወጥ እንደሚችልም አምባሳደር ሬድዋን አስታውቀዋል።

ቀጠናው እየተፈተነ ባለባቸው ጉዳዮች ላይ የቻይናን ድጋፍ በአዎንታዊ መልኩ እንደሚያዩና የተቀናጀው ተግባር ለውጥ ሊያመጣ እንደሚችል ተናግረዋል።

ቻይና የጋራ ጥቅምን መሠረት ያደረጉና ከአፍሪካ ጋር እያከናወነቻቸው ያሉ የትብብር ሥራዎችን አጠናክራ እንድታስቀጥልም ጥሪ አቅርበዋል።

ዛሬም ቀጥሎ በሚካሄደው ኮንፈረንስ ኢትዮጵያን ጨምሮ የአፍሪካ ቀንድ አገራት ተወካዮችና የቻይና ልዑካን እየተሳተፉ ይገኛሉ። የሀገራቱ ተወካዮች ቻይና በአፍሪካ ለምታደርገው ሁለንተናዊ ድጋፍ ምስጋና አቅርበዋል።

ኮንፈረንሱ የአፍሪካ ጉዳይ በአፍሪካዊ መንገድ በአፍሪካውያን መፈታት እንዳለበት የሚደግፍ ሀሳብ የሚራመድበት ሲሆን፤ ለዚህ ደግሞ ቻይና ግንባር ቀደም ሚና ትወጣለች ተብሎ ይጠበቃል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## በአሸባሪው ሕወሓት ጉዳይ የዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ዝምታ ከትዝብት ባለፈ ከፍ ያለ የሞራል ጥያቄ ያስነሳል!

የሰብዓዊነት ጉዳይ እያንዳንዱን ጤነኛ ሰብአዊ ፍጡር የሚመለከት አጀንዳ ነው። ከፍ ካለ የሞራል እሴት ጋር የሚቆራኝ ፤ ፍጥረታዊ ማንነትን ከመረዳት የሚመነጭና ለዚሁ ማንነት መገዛትን የሚያመላክት ነው። ከፍጥረታዊ ማንነት የሚቀዳን ድምጽ ሰምቶ ፍጥረታዊ ምላሽ መስጠትን የሚመለከት ነው።

ስለ ሰብዓዊነት ለማሰብ በተለየ ሁኔታ በጉዳዩ ላይ ኤክስፐርት መሆንንም አይጠይቅም፤ ስለ ሰብአዊነት ለመናገር በሞራል እሴት የተገራ ሰውነት በቂ ነው። ያልተገራ ሰውነት ከሚፈጥረው ራስ ወዳድነት እና ስግብግብነት ነፃ መውጣትንም የሚሻ ነው።

ይህ ባልሆነበት ሁኔታ ስለ ሰብዓዊነት የሚሰሙ ዲስኩሮች ሆኑ በሰብአዊነት ስም የሚከናወኑ ያልተገቡ ተግባራት በማህበረሰብ ውስጥ ያሉ ሰብአዊ እሴቶችን ከማደብዘዝ ባለፈ ሊኖራቸው የሚችለው ፋይዳ እዚህ ግባ ሊባል የሚችል አይደለም። እንዲያውም በእሴቶቹ ዙሪያ የአስተሳሰብ መደናገርና ግራ መጋባት ሊወልዱ ይችላሉ።

ባለንበት ዘመን በዓለም አቀፍ ደረጃ ሰብአዊነትን የራሳቸው አጀንዳ ብቻ አድርገው የሚመለከቱ ይህንን የሚያቀነቅኑ ሀገራት፣ ተቋማትና ቡድኖች አሉ።እነዚህ ሀገራት ፣ተቋማት እና ቡድኖች አንድም ሰብአዊነትን የራሳቸው የብቻ አጀንዳ ማድረጋቸውን ፤ ከዚህም ባለፈ በሰብአዊነት ሽፋን በሌሎች ላይ ፍላጎቶቻቸውን መጫን የዕለት ተዕለት ተግባራቸው ከሆነ ውሎ አድሯል።

ይህም የሀገራትን የተረጋጋ ማህበራዊ ህይወት ከማመሳቀል ጀምሮ ሀገራትን እስከ ማፍረስ የዘለቀ ተግባራትን በአደባባይ ሲፈጸሙ እንዲስተዋል አድርጓል፤ ዛሬም ሲፈጸሙ እየታየ ነው። የሰብዓዊነት ጉዳይ ሰብዓዊ አጀንዳነቱ ቀርቶ የመንግስታትን እጅ መጠምዘዣ ዋነኛ የፖለቲካ መሳሪያም ከሆነ ሰንብቷል።

በተለይም ራሳቸውን ለመሆን የሚጥሩ ሀገራት መንግስታትን ራስን የመሆን መሻት በማደናቀፍ የእነርሱ ፍላጎት ተሸካሚ ለማድረግ ሰብዓዊነትና ከሰብአዊነት ጋር ተንሰላስለው ለሚነሱ አጀንዳዎች ከፍ ያሉ አቅም እየፈጠሩላቸው ይገኛሉ። በሰብዓዊነት ስም በተገመዱ ገመዶች የታሰሩ፤ በሰብዓዊነት ስም በተጫነ ቀንበር የጎበጡ ሀገሮችና ሕዝቦች ብዙ ናቸው።

በኛም ሀገር ቢሆን በተለይም ከለውጡ ማግስት ጀምሮ ከሰብዓዊነት ጋር በተያያዘ የሚነሱ ጉዳዮች ከዚህ ዓለምአቀፋዊ እውነታ ያፈነገጡ አይደሉም። በሰብዓዊነት ስም የለውጡን ኃይል አንገት ለማስደፋትና ለውጡን ለማደናቀፍ ለሰብአዊ መብቶች ያለኝ ከሚሉ ሀገራት፣ተቋማት እና ቡድኖች የደረሰብን ጫና/ጣልቃ ገብነት ከፍ ያለ ነው።

ይህ ጫና በአሸባሪ ቡድኖች በአደባባይ የሚከናወኑ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን እንዳላየ ከመመልከት ጀምሮ፤ መንግስት ህግና ስርአትን ለማስከበር የሚወስዳቸውን ርምጃዎች ከተልዕኳቸው ባፈነገጠ መልኩ የፖለቲካ አጀንዳ እያደረጉ መንግስት ሀገርና ሕዝብን የመጠበቅ ህገመንግስታዊ ኃላፊነቱን እንዳይወጣ የሚገዳደሩ ናቸው።

ከዚህ ባለፈ መንግስት ስለ ሰላም የሚወስዳቸውን ርምጃዎች አሳንሶ ማየት ፤ ከመንግስት የሰላም ቁርጠኝነት ይልቅ፤ በሰብአዊነት ስም የተቃዋሚ ኃይሎችን አጀንዳ ወደ አደባባይ ማምጣት እና ጫና መፍጠር ፤ በሰብዓዊነት ስም የሀገሪቱን ሉአላዊነት መደፋፈር ተደጋግሞ የተስተዋለና ዛሬም እየተስተዋለ ያለ እውነታ ነው።

መንግስት አሸባሪው ሕወሓት በእብሪት ከለኮሰው ጦርነት ማግስት ጀምሮ ሰብአዊነትን መሰረት በማድረግ ለትግራይ ሕዝብ የርዳታ አቅርቦቶች እንዲደርሱ ረጅም መንገድ መሄዱ ፤ በዚህም ከፍ ያለ ዋጋ መክፈሉ ይታወሳል። በተለይም ቡድኑ ለህዝብ የተላኩ የእርዳታ አቅርቦቶችን፤ አቅርቦት ጭነው የሄዱ መኪኖችንና ለዚሁ ተግባር የተላከ ነዳጅ ለጦርነት ማዋሉ የሚታወስ ነው።

ቡድኑ በአደባባይ በማን አለብኝነት ያደረገውን ይህንን ተግባር ሰብዓዊነትን የራሳቸው አጀንዳ ብቻ አድርገው የሚመለከቱ ይህንን የሚያቀነቅኑ ሀገራት፣ ተቋማት እና ቡድኖች ለማውገዝ አልፈቀዱም፤ ከዚህ ይልቅ እንዳላየና እንዳልሰማ መሆንን መርጠዋል። ይህ ያልተገባ ተግባራቸው የትግራይ ሕዝብንም ሆነ ሀገርን እንደ ሀገር እያስከፈለ ያለው ዋጋ ቀላል የሚባል አይደለም።

ቡድኑ ዛሬም በተመሳሳይ መንገድ የርዳታ አቅርቦቶችን ይዘው ወደ ክልሉ የገቡ መኪኖች እንዳይወጡ በማድረግ፤ ለህዝብ የተከፋፈሉ የእርዳታ አቅርቦቶችን በተለያዩ አስገዳጅ ሁኔታዎች ከሕዝቡ በመሰብሰብ ፤ ከዛም ባለፈ በቤተሰብ ደረጃ ኮታ በመጣል ለወጣቶች ያለ ፈቃዳቸው ስልጠና በመስጠት ራሱን ለጦርነት እያዘጋጀ ይገኛል።

ይህንን ጸሀይ የሞቀው እውነታ ዓለም አቀፉ ኅብረተሰብ በተለይ ደግሞ ሰብዓዊነትን የራሳቸው አጀንዳ ብቻ አድርገው የሚመለከቱና ይህንን የሚያቀነቅኑ ሀገራት፣ ተቋማትና ቡድኖች እስካሁን ለማውገዝ ፈቃደኛ አለመሆናቸውና እንደቀደመው ጊዜ ዝምታን፣ መምረጣቸው ከትዝብት ባለፈ ከፍ ያለ የሞራል ጥያቄ የሚያስነሳ ነው!

ይህ ዝምታቸው ለአሸባሪው ሕወሓት በጥፋት ተልዕኮህ ግፋበት የሚል መልእክት የሚያስተላልፍም በመሆኑ ድርጊቱን ፈጥነው በአደባባይ ሊያወግዙትና ከድርጊቱ እንዲቆጠብ ጫና ሊፈጥሩበት ይገባል!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

## የንግዱ ማኅበረሰብ ያልተገባ ጥቅም ከማጋበስ ወጥቶ ስለ ሀገርና ሕዝብ ሊያስብ ይገባል!

አምኃየስ

በሀገሪቱም ይሁን በዓለም አቀፍ ደረጃ በተከሰቱ ሁነቶች ምክንያት የሸቀጥና የምግብ ፍጆታዎች ዋጋ በየጊዜው እየጨመረ ይገኛል:: በተለይ መሰረታዊ በተባሉ የምግብ ፍጆታዎች ላይ በየቀኑ በሚባል ደረጃ ዋጋቸው እየናረ ነው:: የዋጋዎች መጨመር ደግሞ ተጠቃሚውን ወይም ሸማቹን ህብረተሰብ በከፍተኛ ሁኔታ እያስጨነቀው ይገኛል::

በሀገሪቱ እየሆነ ያለውን የዋጋ ግሽበት ደረጃ ለመረዳት የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ በ2014 ዓ.ም ያወጣቸውን ወርሃዊ ሪፖርቶች አለፍ አለፍ ብሎ በወፍ በረር መመልከት ያስፈልጋል:: በኤጄንሲው ሪፖርት መሰረት በ2014 ዓ.ም የመስከረም ወር አጠቃላይ የዋጋ ግሽበት ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር 34 ነጥብ 8 በመቶ፤ የታኅሣሥ ወር አገራዊ የዋጋ ግሽበት 35 ነጥብ አንድ በመቶ ጭማሪ የምግብ ዋጋ ግሽበት ደግሞ 41 ነጥብ 6 በመቶ፤ የመጋቢት ወር የዋጋ ግሽበት ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወር ጋር ሲነጻጸር በ34 ነጥብ 7፤ የግንቦት ወር 36 ነጥብ 6 በመቶ ጭማሪ ማሳየቱን ገልጿል። ይህ የምግብ እና የሸቀጣ ሸቀጦች ዋጋ መናር የሸማቹን ማህበረሰብ የመግዛት አቅም በማዳከም የሀገሪቱን ሁለንተናዊ እንቅስቃሴዎች እንደሚያዳክመው ቅንጣት ያህል የሚያጠራጥር አይደለም::

በጊዜ ሂደት የሸማቹ የመግዛት አቅም እየተዳከመ ሲሄድ ሸማቹ ማህበረሰብ ወደ ዝርፍያና ሁከት መግባቱ አይቀሬ ነው:: ከነዋሪው ጋር የሚመጣጠን የኑሮ ቀመር ባለመዘርጋቱ ምክንያት ነጋዴውም ሆነ ሌላው አገልግሎት ሰጪ እንዳሻው በሚጨምረው ዋጋ በቀን ሶስቴ ከመብላት ወደ አንድ ጊዜ መብላት የሚሸጋገረው ሰው እየበዛ እንደሚመጣ መገመት አያዳግትም::

አንድ የዓለም አቀፍ ጥናት እንዳመላከተው በአንጎላ፣ ቱርክ ፣ ብራዚል እና በሲሪላንካ ያለው የኑሮ ውድነት አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሷል:: ይህ ጥናት በኢትዮጵያ ያለቀውን የኑሮ ውድነት አላካተተም:: ይሁን እንጂ በጥናቱ የዋጋ ግሽበት ያሰጋቸዋል የተባሉት ሀገራት የዋጋ ንረት እና የኢትዮጵያን በንጽጽር ስንመለት በኢትዮጵያ እየተስተዋለ ያለው የዋጋ ንረት ስጋት አለባቸው ከተባሉት ሀገራት የሚበልጥ እንጂ የሚያንስ አይደለም ::

በአንድ ሀገር ውስጥ የሚኖር ዜጋ በችግር፣ በደስታና በሌሎች ጉዳዮች ተረዳድቶ መኖር እንዲሁም የሚኖርበትን ሀገር ከጠላት የመጠበቅ ግዴታ አለበት:: በተጨማሪም በመረዳዳት መንፈስ ለሀገር ብልፅግናና እድገት መስራት ይኖርበታል::

**«እኔ ብቻ ልጠቀም» በሚል መንፈስ የተበከሉ ሰዎች እየተበራከቱ በመምጣታቸው የብዙኃኑን ኑሮ በከፍተኛ ሁኔታ ሲያመሰቃቅለው እየተስተዋለ ነው። የዚህ ሀገራዊ ችግር በጊዜ መቅረፍ ካልተቻለ የሀገሪቱን ሁለንተናዊ ውድቀት የሚያፋጥን እና ሀገርን አለመረጋጋት ውስጥ የሚከት ይሆናል**

በሀገራችን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የሚታየው እውነታ ግን ከዚህ የተገላቢጦሽ እየሆነ ነው። ‹‹እኔ ብቻ ልጠቀም›› በሚል መንፈስ የተበከሉ ሰዎች እየተበራከቱ በመምጣታቸው የብዙኃኑን ኑሮ በከፍተኛ ሁኔታ ሲያመሰቃቅለው እየተስተዋለ ነው:: የዚህ ሀገራዊ ችግር በጊዜ መቅረፍ ካልተቻለ የሀገሪቱን ሁለንተናዊ ውድቀት የሚያፋጥን እና ሀገርን አለመረጋጋት ውስጥ የሚከት ይሆናል::

የኑሮ ውድነቱ ሲነሳ ከምግብ ጀምሮ ያልጨመረ ነገር አለመኖሩ ሲታሰብ ይህ ሁኔታ ወዴት እያመራ ይሆን? የሚለው ጉዳይ ሁሉንም ሰው በውስጡ እንዲያስብ አድርጎታል:: በተለይ ደግሞ የገንዘብ የመግዛት አቅም እየተዳከመ መምጣት ጉዳዩን ትኩረት እንዲሰጠው ያደርገዋል::

ከሸቀጦች መወደድ በላይ የሚፈለጉት ምርቶች አለመገኘት የስጋቱን ሁኔታ ከፍ ያደርገዋል:: ገንዘብ ያለው ሰው በራሱ የኑሮ ሁኔታ ቢጠየቅ ምንም ከሌለው ሰው እኩል ኑሮ እየፈተነው ስለመሆኑ በልበ ሙሉነት ያወራል:: ለዚህ ደግሞ የገንዘብ የመግዛት አቅምና የሸቀጦች በገበያው አለመገኘት በዋነኛነት ተጠቃሽ ናቸው::

ሀገሪቱ አብዛኛውን ምርት ከውጭ የምታስገባ ቢሆንም በሀገር ውስጥ ምርት ደግሞ የምትሸፍናቸው ብዙ የሸቀጥ ምርቶች አሉ:: የበለጠ አሳሳቢው ጉዳይ ግን ከውጭ የሚገባውም ሆነ በሀገር ውስጥ የሚመረተውም የምግብ እና ሌሎች የፍጆታ እቃዎች በየጊዜው የዋጋ ጭማሪ ማድረጋቸው ነው::

በዓለም አቀፍ ደረጃ የነዳጅ ዋጋ መወደድ ተከትሎ በሀገር ውስጥም የነዳጅ ዋጋ መጨመሩ ይታወቃል:: ይህም የሸቀጥ ገበያ ዋልታ ረገጥ እንዲሆን አድርጎታል። ትንሽ ሰበብ የሚፈልገው የንግዱ ማህበረሰብ ገና በቀጣይ ነዳጅ ሊጨምር ይችላል በሚል ግምት ሁሉም ምርቶች ላይ አግባብ ያልሆነ ጭማሪ ማድረጋቸው የተለመደ ሆኗል።

ለዚህ ሕገወጥ አካሄድ ተገቢው እርምጃ አለመወሰዱ ለችግሩ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ሆኗል። ለኑሮ ወድነቱ ተጨማሪ ምክንያት እየሆነ ይገኛል። በቀጣይም ችግሩን ለመቅረፍ ለሚደረጉ ጥረቶች ዋነኛ ተግዳሮት እንደሚሆን ይታመናል::

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ሰሞኑን በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በኑሮ ውድነት ዙሪያ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ እንደገለጹትም፤ ባለፉት ስድስት ወራት መንግሥት 30 ቢሊዮን ብር በመመደብ የኑሮ ውድነቱን ለማረጋጋት ሠርቷል።

የምርት እጥረትና የፍላጎት መጨመር፣ የንግድ ሥርዓቱ መዛባት፣ ምርት እያለ ማቅረብ አለመቻል፣ ግጭትና የገንዘብ አጠቃቀም ጉድለት ለኑሮ ውድነቱ እንደ ዋነኛ ምክንያትነት ጠቅሰዋል::

በዓለም ደረጃ ያለውን የዋጋ ንረት መገንዘብ ተገቢ መሆኑን ፤ በበርካታ ሀገራት ከፍተኛ የዋጋ ንረት እየታየ እንደሚገኝ አመልክተዋል:: በኢትዮጵያ ያለው የዋጋ ንረት 33 በመቶ መሆኑን ጠቁመዋል።ቁጥሩ ትንሽ ቢመስልም እያስከተለ ያለው ጫና ከፍተኛ ነው።

የኑሮ ውድነቱ በሀገሪቱ በተለይም በዝቅተኛ የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ እያሳደረ ያለውን ጫና ለመቋቋም በመንግስት በኩል የተለያዩ ስራዎችን እንደሚሰሩ አመልክተው፤ መላው ህዝብም ችግሩን በመፍታት ሂደት ውስጥ ንቁ ተሳታፊ መሆን እንደሚጠበቅበት ማሳሰባቸው ይታወሳል።

በርግጥ ቀደም ሲል እንደ ሀገር ከገባንበት ፈተናና ይዘናቸው ከመጣናቸው የቤት ስራዎች አንጻር አሁን ያለንበት ሀገራዊ ቁመና ለኑሮ ውድነቱ ያለው አስተዋጽኦ ከፍ ያለ እንደሚሆን መገመት የሚከብድ አይሆንም።

በዚህ ተጨባጭ እውነታ ላይ በዓለም አቀፍ ደረጃ እያጋጠሙ ያሉ ተግዳሮቶች ሲደመሩበት የፈተናው አቅም እንደ ሀገር ተገዳዳሪ ሆኗል። ከዚህ አንጻር ዜጎች ሁሉ በተለይም የንግዱ ህብረተሰብ ያልተገባ ጥቅም ከማጋበስ ወጥቶ ስለ ሀገርና ህዝብ ሊያስብ ይገባል ።ይህንንም የማድረግ የዜግነት ከዛም በላይ የሞራል ግዴታ አለበት ! መልዕክቴ ነው:: ሰላም

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ

## በውሸት ትርክት የተጉሳቆለችውን ሀገራችንን በእውነት እና በፍቅር እናጽና!

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ውሸት ምን ያህል ሀይል እንዳላት አሸባሪው ሕወሓት የኔ ዘመን ባለታሪክ ነው። እኩይ ባለታሪክ። ትላንት ዛሬና ነገ የራሳቸው የሆነ የእውነት የፍትህና የህቅ ሚዛን አላቸው። በዚህ የጊዜ አብራክ ውስጥ ሙሉ ሆኖ ማለፍ ደግሞ የሁሉም ነፍሶች ግዴታ ነው። ምክንያቱም ሰውነት ለሌሎች መልካም የመሆን ስራት ነውና። ይሄ እውነት የሌላቸው አንዳንድ ጎደሎ ነፍሶች አሉ። በመኖራቸው ሌሎችን የሚያስጨንቁ፣ በሰውነታቸው ለሌሎች መከራ የሆኑ ነፍሶች። ከነዚህ ነፍሶች ውስጥ አንዱ ደግሞ የአሸባሪው ሕወሓት ነፍስ ነው።

ቡድኑ እንደ ሰው አካልና ነፍስ አለው ግን ይሄንን አካልና ነፍሱን ሌሎችን ከመጥቀም ይልቅ ሌሎችን በመጉዳት ያበለጸገው ነው። ከዚህ ጎደሎ ማንነቱ ውስጥ በውሸትና በማስመሰል የታጀበውን ራቁት ማንነቱን ማንሳት ይቻላል። ከዚህ ጎደሎ ማንነቱ ውስጥ በክፋትና በተንኮል የተራመዳቸውን እኩይ ርምጃዎቹን መጥቀስ ይቻላል። የሰው ልጅ ከሁሉም ትልቁን እውነትን በሰውነቱ ላይ ማንገስ ካልቻለ ሰው የመሆን ተፈጥሮው እዛ ጋ ያበቃል።

ቡድኑ ለአመታት ብዙ ውሸቶችን ነግሮናል። በነዚህ ውሸቶች ውስጥ ደግሞ እንደ ሀገር ከመጠውለግና ከመበላሸት ባለፈ ያፈራነው መልካም ፍሬ አልነበረም። በየትኛውም ዘመን፣ ለየትኛውም ስብዕና ውሸት ትርፍ የለውም። አንዳንዶች ዋሽተው ያስታርቃሉ። እንደ ሕወሓት ያሉ ጨካኞች ግን ዋሽተው ያጣላሉ። የዛሬዋ ኢትዮጵያ በሕወሓት ብዙ ውሸት የተፈጠረች ናት። በሀገርና ህዝብ ላይ የሚደረግ ውሸት የመጨረሻው የጭካኔ ማሳያ ነው። ሀገር ሁልጊዜም እውነት መሆንን ትሻለች።

የአሸባሪው ሕወሓት የሀሰት ጉዞ ስልጣንን ከማፍቀር የጀመረ ጉዞ ነው። በውሸትና በማስመሰል ካልተራመደ ህዝብ ወዶና ፈቅዶ ስልጣን ላይ እንደማያቆየው ያውቃል። በዚህም ውሸት እየፈጠረ ህዝብን ከህዝብ አባልቷል ። ውሸትና ሕወሓት የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጾች ናቸው። አንዳቸው ያላንዳቸው አይኖሩም ። ውሸት አባትሽ ማነው ቢሏት ሕወሓት እንደምትልና ሕወሓትም ባለውለታህ ማነች ቢሉት ውሸት እንደሚል ተጠራጣሪ ይኖራል ብዬ አላስብም።

ይሄ የሰብዐዊነት ዝቅጠት ነው። በድሀ ሀገርና በህዝብ ላይ መጨከን ምን የሚሉት ፈሊጥ እንደሆነ አልደረስኩበትም። እንዴት አእምሮ ያለው ለዛ ውም መሪ የሆነ ቡድን ሀያ ሰባት አመት ሙሉ ሀገርና ህዝብን ይዋሻል? በሕወሓት ልብ ውስጥ ሀገርና ህዝብ የሉም ። በልቡ ውስጥ ሀገሩን የፈጠረ ሰው ሀገር የሚያጸና እንጂ ሀገር የሚያፈርስ፣ ታሪክ የሚያበላሽ ሀሳብ አይኖረውም። በአእምሮው ውስጥ ህዝብ የፈጠረ ሰው ትውልድ የሚያጀግን እንጂ የሚያሸማቅቅ እሳቤ አይኖረውም።

ውሸት የክህደት የመጀመሪያው እርምጃ ነው። ሕወሓት በየቀኑ ሀገሩን እንደካዳት ነው። በየቀኑ ህዝቡን እንደ ዋሸ ነው። ዛሬ ላይ ዘለን መሻገር ያቃተን ገደል እንኳን ሕወሓት በውሸት የቆፈረው ገደል ነው። ለቡድኑ እውነት እንጂ ውሸት ምኑም አይደለም። በትንሽ ውሸት ሀገር በጥብጦ ያውቃል። የህዝቦችን የዘመናት ፍቅር በራስ ወዳድነት በጠነሰሳት ትንሽዬ ሀሰት ችግር ውስጥ ከቷል ። እንሆ ዛሬም የውሸት ትርክቶቹን እንደቀጠለበት ነው።

ኢትዮጵያዊነት ምን አይነት መልክ እንደነበረው በደንብ አውቃለሁ። በኢትዮጵያዊነት ላይ የፍቅርን ዋጋ የቱን ያህል እንደሆነም አውቃለሁ። ከሕወሓት በፊት የነበረችው ኢትዮጵያ በአባቶቻችን የፍቅርና የህቅ ሚዛን የተሰፈረች፣ በጽናት የተገመደች ነበረች። ይሄ መልክ ይናፍቀኛል። ይሄ ህቅ... ይሄ ሰብዕና ይታወሰኛል። ከሕወሓት በኋላ ሁሉም ነገር ሌላ ሆነ።

> **ሀገር አስተሳሰብ ናት... ሀገር የእውነት ሙዳይ ናት። ውሸት በሆንን ቁጥር እያጉሳቆልናት እንሄዳለን። እውነት በሆንን ቁጥር ደግሞ እያጸናናት እንሄዳለን። ሀገራችንን በእውነት መፍጠር የሁላችንም ግዴታ ነው**

የአባቶቻችን አደራ ተበላ። አንድነታችንና ህብረታችን በስልጣን ጥመኞች አደፈ። ፍቅራችንና መደጋገፋችን በራስ ወዳድ ቡድኖች እንዳልነበረ ሆነ። በጣም የሚገርመው ደግሞ ዛሬም ድረስ በነዚህ ወሮበሎች መሰቃየታችን ነው። ኢትዮጵያዊ ሆኖ በሕወሓት የሀሰት ጅራፍ ያልተገረፈ የለም። ቡድኑ ከትላንት እስከዛሬ የኢትዮጵያ ጠር ነው። እንደ ሀገርም ሆነ እንደ ግለሰብ ብዙ ነገር አሳጥቶናል።

የሕወሓት ቡድን በእውቀት ሳይሆን በውሸት፣ በምክንያት ሳይሆን በሽፍጥ ነው ሀገር ሲመራ የነበረው። በዚህም የዛሬዋን ጉስቋላ ሀገር ፈጥሯል። ሀገር በእውቀት ስትመራና በሽፍት ስትመራ አንድ አይደለም። በሽፍጥ ስትመራ እውቀት ሁልጊዜም መዳረሻው ጥፋትና ውድቀት ነው ።

የዛሬ መከራዎቻችን፣ የዛሬ መገፋፋታችን እነዛ የሽፍጥ አስተሳሰቦች በእኔነት ስሜት ያበዱ እሳቤዎች የፈጠሯቸው ናቸው። እኔና እናንተ እንኳን የእነዛ አስተሳሰቦች ውጤቶች ላለመሆናችን መተማመኛ የለንም ። ይሄ አያናድድም ትላላችሁ? ዛሬ ላይ ብልሽትሽታችን የወጣው እኮ ያ እኩይ አስተሳሰብ ስለተጫነብን ነው። ዛሬ ላይ ውጥንቅጣችን የወጣው እኮ ትላንት ላይ በተነገረን የውሸት ወሬ ነው። የሕወሓት የሴራ ፖለቲካ በእያንዳንዳችን ቤት ፍሬውን አፍርቶ አለ...ይሄ ፍሬ አፍርቶ እንዳይባዛ ዛሬ ላይ በእውነት ልናሸንፈው ይገባል። ዛሬ ለሁላችንም መልካም ቀን ነው።

ትላንትን አሸንፈን አዲስ ታሪክና አዲስ ማንነት የምንፈጥርበት ጊዜ ላይ ነን። ሕወሓትንና አስተሳሰቡን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ጥለን አዲስ ሀገርና አዲስ ትውልድ የምንፈጥርበት ሰሞን ላይ ነን። ሁላችንም ለራሳችንም ሆነ ለሌሎች ስንል ይሄን መልካም የለውጥ ጊዜ መጠቀም ይኖርብናል ።

ሀገር አስተሳሰብ ናት... ሀገር የእውነት ሙዳይ ናት። ውሸት በሆንን ቁጥር እያጉሳቆልናት እንሄዳለን። እውነት በሆንን ቁጥር ደግሞ እያጸናናት እንሄዳለን። ሀገራችንን በእውነት መፍጠር የሁላችንም ግዴታ ነው። በሕወሓት የውሸት ትርክት የቆሸሸችውን ሀገራችንን በእኛ የእውነት ፍቅር ልናነጻት ይገባል።

መርህ አልባ ስሜታዊ እሳቤ ለሀገር እጅግ አደገኛ የሆነ ነገር ነው። ሕወሓት ከትላንት እስከዛሬ ሀገርና ህዝብ ሲመራ የነበረው በዚህ ቁመና ውስጥ ሆኖ ነበር። በጣም የሚገርመው ደግሞ ዛሬም በዚህ ቁመና ውስጥ መሆኑ ነው። ለዚህም ነው በውሸትና በማስመሰል የተካነው። ለዚህም ነው በንጹሀን ሞትና መፈናቀል ስልጣን ለመያዝ የሚታትረው።

ሀገር በውሸት ስትመራ ትውልድ የውሸት ሀይልን ነው የሚያመነጨው። የዘራነውን ስለ ምናጭድ ሌላ ምኞትና ራዕይ አይኖረንም ቢኖረን እንኳን ዋጋ ያስከፍለናል። ዛሬ ላይ በዚህ በጠላት ቡድን በተዘራብን ዘር ነው ከለውጥ ይልቅ ነውጥ፣ ከፍቅር ይልቅ ጥላቻ ወርሶን ያለቦታችን የቆምነው።

ለዚህም ነው ከመነጋገር ይልቅ ጎራ መፍጠር፣ ከመሞጋገስ ይልቅ መተቻቸት ግብራችን የሆነው። ለዚህም ነው ከይቅርታ ይልቅ በቀል፣ ከእውነት ይልቅ ማስመሰል የገነነብን። ሕወሓት ትውልዱ ላይ መርዝ ነው የረጨበት። ያለፉት ሀያ ሰባት አመታት ለኢትዮጵያውያን የመከሰር ዘመናት ነበሩ።

ትውልዱ ቀና እንዳይል በውሸት ትርክት የተተበተበበት። በተጠናና በተመረመረ መርዛም ሀሳብ ታሪክ የተበላሸበት ዘመን ፍዳ። ዛሬም በዚህ እውነት ውስጥ ነን። ውሸት ለሕወሓት ምኑም አይደለም። ያደገበትና ጥርሱን የነቀለበት ነው። አንዳንድ ጊዜ የሕወሓትን ውሸት ሳደምጥ የሰው ልጅ በዚህ ልክ መዋሸት መቻሉ ያስደንቀኛል።

በሕወሓት ውሸት ውስጥ የሚገርም ድራማዊ ማስመሰል አለ። የበግ ለምድ ለብሶ እኔ የሰላም ሀዋርያ ነኝ ተከተለኝ ሊልህ ይችላል። ፍጹም እንዳትጠራጠር በሚያደርግ መልኩ ሊያሳምንህ ይችላል። ግን ሁሉም ድርጊቶቹ ከውሸት የዘለለ አንድም እውነትነት የሌላቸው መሆናቸው ነው።

ቡድኑ ስላልኖረበት የእውነትን ዋጋ አያውቀውም። በውሸትና በማጭበርበር ምን ያህል እንደተራመደ ያለፉት የስልጣን ዘመኑ በቂ ማስረጃዎች ናቸው ። በዚህ ባሳለፍነው አንድ አመት ውስጥ እንኳን ጉድ የሚያስብል ነጭ ውሸት እየዋሸ ሊያሳምነን ሲሞክር እንደነበር ሁላችንም እናውቀዋለን።

በአሻባሪው ሕወሓት ልብ ውስጥ እውቀትና አመክንዩ ሀሳብ የለም። ሁሌም የሚራመደው በውሸት ነው። ከክፋት ባለፈ ቁም ነገር የማይሰሩ ጸዐዳ እጆች አሉት። ለእውነት የሰነፈ ለማስመሰል የበረታ ረጅም ምላስ አለው። ሰብዐዊነት ምኑም ነው። ብቸኛ ደስታው በሌሎች ሞትና ጉስቁልና ስልጣን መያዝ ነው።

በዚህ አንድ አመት ውስጥ እንኳን በርካታ የውሸት ዜናዎችን ስንሰማ ነበር። ሆን ብሎ ፈጥሮ የሚያወራቸው የሀሰት ወሬዎች በርካታ ናቸው። በአፋርና በአማራ ክልሎች በአደባባይ በንጹሀን ላይ የፈጸመውን አሰቃቂ ወንጀል ያልፈጸመው ያህል እንደ ተበዳይ ለአለም አቀፉ ማህበረሰብ የሚጮኸው እሱ ነው። ከፍተኛ ቁጥር ያላቸውን ዜጎች ከቤት ንብረታቸው አፈናቅሎ ሜዳ ላይ እያሳደረ ተበደልኩ ባዩ እሱ ነው። ህጻናትን ያለርህራሄ እየጨፈጨፈ፣ ወጣት ሴቶችን እየደፈረ ተጠቃሁ የሚለው እሱ ነው።

ቡድኑ ምን አይነት ማንነት እንዳለው ያለፉትን ሀያ ሰባት አመታት ትተን ያለፉትን አስራ ሁለት ወራቶች ማየቱ ብቻ በቂ ነው። በማይካድራና በአፋር የሆነው መቼም የሚረሳ አይደለም። ዜጎች በማንነታቸው እየታደኑ እንደከብት የሚታ ረዱበትን ጊዜ አሳልፈናል። በሰሜን ወሎ፣ በጎንደር በዋግ ህምራ፣ በአፋር ክልሎች እና በሌሎችም የሀገሪቱ ክፍሎች ያሉትን የሕወሓት ተጠቂ ንጹሀን ማየቱ ዛሬ ላይ ይሄን ቡድን ለፍርድ ለማቅረብ በቂ ማስረጃ ነው።

አለም አቀፉ ማህበረሰብ ግን የሕወሓትን የድረሱልኝ ጩኸት እንጂ የህዝቡን የድረሱልኝ ጩኸት ለመስማት ዝግጁ አይደለም። በጣም የሚገርመው ደግሞ አለም ሕወሓት ምን አይነት ማንነት እንዳለው እያወቀች ግን ዛሬም ከውሸትና ከማስመሰል ድራማው ጎን እንደቆመች መሆኗ ነው ።

አሜሪካና መሰል ሀያላኖቹ ቡድኑ ዝም ሲል ዝም የሚሉ ሲጮህ አብረው የሚጮሁ ሆነዋል። ለዚህም በቡድኑ ወደ ስልጣን መም ጣት የሚያተርፉት ብዙ ትርፍ ስለ መኖሩ ብዙም መጠየቅ የሚያስፈልገው ጥያቄ አይደለም። እኛ ግን ለአሻባሪው ሕወሓት የውሸት ዜና ቦታ ሳንሰጥ ሀገራችንን በእውነትና ከዚህ በሚመነጭ ቁርጠኝነት ለማገልገል እንነሳ እላለሁ።

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## ኢትዮጵያን የሳይበር ጥቃት ምን ያህል ያሰጋታል?

**ዳግም ከበደ**



በዓለማችን ላይ የሳይበር ደህንነት ጉዳይ ቀዳሚውና ወሳኙ እንደሆነ ይነገራል። በኢትዮጵያም እየተፋጠነ የመጣውን የዲጂታል ሽግግር አስመልክቶ እንደ ቀሪው ዓለም ወሳኝ መሆኑ አጠያያቂ አይደለም። የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲን ጨምሮ በዘርፉ ጉልህ ድርሻ ያላቸው አካላት "የሳይበር ደህንነት" በአገራችን ቀዳሚውን ትኩረት የሚሻበትን ጉዳይ ሲያስቀምጡ የመጀመሪያው ምክንያታቸው በኢትዮጵያ ዲጂታላይዜሽን ማደግ እንደሆነ ይናገራሉ። ሌላው አመክንዮ ደግሞ የሳይበር ምህዳሩ የዘመኑ መወዳደሪያ መሆን መቻሉ፤ የተቋማትና የዜጎች በምህዳሩ የመጠቀም አቅምና ፍላጎት መጨመሩ፤ በሳይበር ምህዳሩ ላይ ዓለም አቀፍ ተጽእኖው መጨመር እንደሆነም ያስረዳሉ። በዚህ ምክንያት በኢትዮጵያ ውስጥ ከመቼውም ጊዜ በተለየ መልኩ ይህ ዘርፍ ልዩ ትኩረትን የሚሻ እንዲሆን አስችሎታል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ባሳለፍነው ሳምንት የህዝብ ተወካይ እንደራሴዎች ያነሷቸውን ጥያቄዎች አስመልክተው ማብራሪያ መስጠታቸው ይታወሳል። በዚህ ወቅት ከዲጂታል ቴክኖሎጂና የሳይበር ምህዳር ጋር በተገናኘም ማብራሪያ የሚሻ ጥያቄ ተሰንዝሮ ነበር። በዋናነት ጥያቄው የሚከተለውን ጭብጥ የያዘ ነበር።

የሳይበር ጦርነት ዓለማችንን እያሳሰበ የመጣ አዲስ የቴክኖሎጂ የጦርነት አውድማ ሆኗል፡፡ የዚህ አይነት ጥቃት በአይን የማይታይ እጅግ በረቀቀ ዘዴ በስውር በርቀት የሚሰነዝር በጥቂት ሴኮንዶች ውስጥ የዒላማዎቹን አሰራር የማዛባት የማወክና የማስተጓጎል ከፍተኛ አቅም ያለው በአገራት መካከል የሚካሄድ ዘመናዊ የጥቃት ዘዴ ነው። ከዒላማዎቹ ዋና ዋና ግዙፍ የልማት፣ የፋይናንስ፣ የመከላከያና የደህንነት ተቋማት ሲሆኑ መዘዙና ጉዳቱም ከፍተኛ መሆኑ የወቅቱ የዓለማችን ዋና የስጋት ጎራ ውስጥ ይመደባል። ለዚህም ነው ጊዜው አገራዊ የሳይበር ደህንነትና የሳይበር ጥቃት የሚባለው፡፡

የዚህ አይነት ጥቃቶችን ለመከላከል የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር በቀደመው ጊዜ በ1999 ዓ.ም ተመስርቷል፡፡ ይህ ተቋም በተለይም ባለፉት አራት ዓመታት በተደረገለት ከፍተኛ ትኩረትና ሪፎርም በሰለጠነ አኩሪና ብቃት ባላቸው ባለሙያዎች፣ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ፤ ተቋማዊ ቁመናና በአሰራር ስርዓት ለውጥ የተሰነዘሩብንን በርካታ የሳይበር ጥቃቶች በአስተማማኝ ሁኔታ መመከትና ማምከን ተችሏል፡፡

የሳይበር ጥቃት ሁሉንም የቴክኖሎጂ ተጠቃሚዎችን ኢላማ አድርጎ የሚሰነዘር በመሆኑ የሳይበር ደህንነት የኢንሳ ብቻ ሳይሆን የሁሉም ተቋማት ትኩረትን የሚሻ በመሆኑ በዓመታዊ እቅዳቸው ተካትቶ እንዲተገበር የአስሩ ዓመት የልማት እቅድ የሳይበር ጥቃትን ሊያካትት ይገባል፡፡ ዘመኑ የዲጅታል ቴክኖሎጂ ነውና የዲጅታል ሉአላዊነታችን በሳይበር ጥቃት እንዳይደፈር የተሟላ ጥንቃቄና ዝግጅት ማድረግ ወሳኝ በመሆኑ በዚህ በኩል ያለው ዝግጅት ምን ይመስላል?

### ምን ዝግጅት ተደርጓል?

ከላይ ከህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንደራሴዎች ከሆኑት ከአንዱ ለተነሳው ጥያቄ ምላሻቸውን ያስቀመጡት ጠቅላይ ሚኒስትሩ "ኢትዮጵያ ላይ ባለፉት 9 ወራት ብቻ 5 ሺ 860 ገደማ የቨርቹዋል ጥቃት ተካሂዷል፡፡ ይህ ማለት በጥቅሉ ስድስት ሺ ጥቃት ደርሶብናል፡፡ በሚሊየን ብር ያጣንበት አለ በቢሊየን ያዳንንበት አለ፡፡ ዋናው ፋይናንሻል ዘርፍ አይ ሲ ቲ መሰረተ ልማት እና በኢንፎርስመነት ኤጀንሲስ ፤ መንግሥት ተቋማት እና ፕሮጀክቶቻችን በብዙ መንገድ ይሞከራሉ" በማለት ያለውን ስጋት ለማብራራት ከመሞከራቸውም በላይ ጥቃቱን ለመከላከልና የዘርፉን አስተማማኝነት ለማረጋገጥ እየተሰሩ ስላሉ ስራዎች ማብራሪያ ሰጥተውበታል።

### አስተዳደሩ ምን ይላል?

የሳይበር ደህንነት ላይ ኃላፊነት ወስዶ በቀዳሚነት የሚሰራው የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር በተወካዮች ምክር ቤት የተነሳውን ጥያቄና የጠቅላይ ሚኒስትሩን ማብራሪያ ተከትሎ የሚከተለውን መረጃ ይፋ አድርጓል። በተለይ በኢትዮጵያ በ11 ወራት ከተሞከሩ የሳይበር ጥቃቶች ከ97 በመቶ የሚልቀውን በማክሸፍ የ1 ነጥብ 4 ቢሊየን ብር ኪሳራ ማዳን መቻሉን ይፋ ያደረገው መስሪያ ቤት የሳይበር ጥቃቱ በፋይናንስ እና የሚዲያ ተቋማት ላይ በብዛት ኢላማ ያደረገ መሆኑም ነው የተናገረው።

የሳይበር ምህዳር በባህሪው ድንበር የለሽና ኢ-ተገማች በመሆኑ ዓለም በዚህ መጠነ-ሰፊና ተለዋዋጭ ወንጀል በየቀኑ በአማካይ 16 ነጥብ 4 ቢሊየን ዶላር ሀብት ታጣለች። የሳይበር ወንጀል በ2015 በዓለም ላይ 3 ትሪሊየን ዶላር ካደረሰው ኪሳራ በእጅጉ እያንሰራራ መጥቶ በ2021 ደግሞ 6 ትሪሊየን ዶላር አሳጥቷል። በየዓመቱ በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ የመጣው ዓለም አቀፍ የሳይበር ወንጀል በ2025 ከ10 ነጥብ 5 ትሪሊየን ዶላር በላይ ሊያሳጣ እንደሚችል ተገምቷል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ፤ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት ሰሞኑን በሰጡት ማብራሪያ በኢትዮጵያ ባለፉት ዘጠኝ ወራት 5 ሺህ 860 የሳይበር ጥቃት ሙከራዎች መደረጋቸውን በማስታወስም፤ በዓለም ላይ በየቀኑ በቢሊዮን ዶላር የሚያሳጣው የሳይበር ጥቃት ለኢትዮጵያም ፈተና መሆኑን ገልጿል። የኢንፎርሜሽን መረብ ደኅንነት አስተዳደር ምክትል ዋና ዳይሬክተር ሰለሞን ሶካ፤ የሳይበር ወንጀል በኢትዮጵያም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣቱን ይናገራሉ። በዚህም በ2011 ዓ.ም 790፣ በ2012 ዓ.ም 1 ሺህ 80፣ 2013 ዓ.ም 2 ሺህ 900 የሳይበር ጥቃቶች መድረሳቸውን ጠቅሰዋል።

በዘንድሮው በጀት ዓመት 11 ወራት ደግሞ 6 ሺህ የሚደርሱ የሳይበር ጥቃት ሙከራዎች መደረጋቸውን ገልጸዋል። በኢትዮጵያ ላይ የተሞከሩ የሳይበር ጥቃቶች ከየት እንደተሞከሩና የወንጀሉን ባለቤቶች በቀላሉ ለመለየት ባይቻልም ያነጣጠሩባቸው ተቋማት መለየታቸውንም ጠቁመዋል።

በሳይበር ጥቃቱ በተለይም በባንክና የፋይናንስ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ላይ ማነጣጠሩን ጠቅሰው፤ የሚዲያ ተቋማትም ኢላማ መደረጋቸውን ተናግረዋል። የመንግሥት ቁልፍ መሰረተ-ልማቶች፣ የፖለቲካ አደረጃጀቶች፣ የፌዴራልና የክልል የመንግሥት ተቋማት እንዲሁም የጤና እና የትምህርት ተቋማትም በርከት ያለ ጥቃት ተሞክሮባቸዋል ተብሏል።

ከተሞከሩ 6 ሺህ የሳይበር ጥቃቶች መካከል ከ97 በመቶ በላይ ሙከራዎችን በማክሸፍ የ1 ነጥብ 4 ቢሊየን ብር ኪሳራ ማዳን መቻሉን ጠቅሰዋል። ሊደርስ የነበረውን አደጋ የማዳን አቅም እየጎለበተ መሆኑን የገለጹት ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ፤ የሳይበር ወንጀል ሁልጊዜም ኢ-ተገማች በመሆኑ መጠንቀቅ እንደሚገባ ከኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ጋር በነበራቸው ቆይታ ገልጸዋል። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ለምክር ቤቱ በሰጡት ማብራሪያ፤ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት ለማስከበር ከመደበኛ የሰራዊት ግንባታ ጎን ለጎን የሳይበር ጥቃትን የሚከላከል አቅም መገንባት እንደሚገባ አጽንኦት ሰጥተዋል።

### ቢግ ዳታ እና ሰሳይበር ጥቃት

እንደ ኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ መረጃ "ቢግ ዳታ ከጊዜ ወደ ጊዜ በከፍተኛ ፍጥነት የሚያድግ በመጠኑ በጣም ትልቅ የሆነ (የተዋቀረ ወይም ያልተዋቀረ) መረጃ" ሲሆን በውስጡም ውስብስብ የሆኑ የዳታ ስብስቦችን የያዘ የመረጃ ክምችት አይነት ነው። ይህ ከፍተኛ መረጃ ክምችት በቆዩ ወይም ባልዘመኑ የመረጃ ቋት (data base) እና በሶፍትዌር ሲስተሞች ሊሰራና ሊከወን የማይችልም ነው።

በተቋማት ውስጥ የዚህን መረጃ ጥራት ወይም አጠቃላይ ሁኔታ በመግለጽ ጥቅም ላይ የሚዉሉ የመረጃዎች መጠን፣ ልዩነት፣ ፍጥነት፣ ትክክለኛነት የሚባሉ መለያዎችን ወይም ባህሪያቶችን ይጠቀማሉ።

በሳይበር ደህንነት የጥቃት መንገዶች መጨመር ጋር ተያይዞ ሚስጥራዊ መረጃን በማስጠበቅ የተቋምን የሥራ ክንውን፣ እድገትና አቋም ማስቀጠል ወይም ማስጠበቅ አስቸጋሪና ከባድ ሊሆን ይችላል። ዴታን ከጥቃት መከላከል ወይም መጠበቅም አንዱና ዋናው በሳይበር ደህንነት ፈታኝ ጉዳይ ነው።

የዚህ ከፍተኛ የሆነ ዳታ መጥፋት ወይም መበላሸት የደንበኛ እምነት ማጣትን፣ ለኪሳራ፣ አለፍ ሲልም የደንበኛ መረጃ ስርቆት ወይም መጥፋትን፣ ለከፍተኛ ኪሳራና አደጋ ሊያጋልጡ የሚችሉ የሲስተም መስተጓጎሎችን ወይም መቋረጦችንም ያስከትላል። ይህ የከፍተኛ መረጃ ክምችት በተሳሳተ ወይም አግባብ በሌለው አካል እጅ ውስጥ ሊገባ ወይም ለተፈጥሮም ሆነ ሰው ሰራሽ አደጋዎች ሊጋለጥ ይችላል።

ከዳታ ጋር የተያያዙ ሥራዎችን ለማከናወን ወይም የሳይበር ደህንነቱን ለማስጠበቅ የሚውሉ የቆዩ ወይም ያልዘመኑ የደህንነት መቆጣጠሪያ ሲስተሞችና ቴክኖሎጂዎች ብቁ ስለማይሆኑ፤ ይህን ትልቅ ይዘት ያለውን ዳታ መቆጣጠር ወይም መቀበል ስለማይችሉ ሊበላሹ ወይም ሊጠፉ ይችላል። በዋናነት ደግሞ በሚከተሉት ምክንያቶች ተጋላጭ ሊሆን ይችላል። በባለሙያ ክህሎት ወይም እውቀት ክፍተት ጋር ተያይዞ ይህ መረጃ ለሌላ ጥቃት ሰለባ ሊሆንም ይችላል። የዳታ ምንጮቹ በጣም ብዙና የተለያዩ የቴክኖሎጂ ውጤቶች ከመሆናቸው አንጻር እያደገ በሚሄድበት ሰዓት ውስብስብነቱ ደህንነቱን ማስጠበቅ ከባድ እንዲሆን ያደርገዋል። ትክክለኛ እና አላስፈላጊ የሆነ ዳታም የመረጃ ክምችትን መፋለስ እና ሥራን እንዲሰናከል ሊያደርግ ይችላል።

የከፍተኛ መረጃ የዳታ ብክለት ከመረጃ አመክንዮ መዛባት እስከ ዳታ መቀላቀል ወይም መቀየር እና መበላሸት የሚደርስ ጉዳት ያስከትላል። ከውስጥ ባለ ሰው ታስቦበትም ይሁን ሳይታሰብበት ሚስጥራዊ የሆኑ መረጃዎች ሊወጡ እና ለስርቆት ሊጋለጡ ይችላሉ። የሳይበር ወንጀለኞች ከከፍተኛ መረጃው ጋር ግንኙነት ያላቸውን ሲስተሞች ክፍተት በመጠቀም ስርቆት ወይም የዳታ ማጥፋት ጥቃቶችን ሊፈጽሙ ይችላሉ። ዳታ በሰዎች ጫና ወይም አሉታዊ ሥራዎች በተጨማሪ በተፈጥሮ አደጋዎች ዳታው ሊበላሽ ይችላል።

### የሳይበር ጥቃት ተጋላጭነት

ከአምስት የህዝብ አገልግሎት ሰጪዎች ከሚጠቀሙባቸው መተግበሪያዎች መካከል ከአራት በላይ የሚሆኑት (82 ከመቶ) የሳይበር ጥቃት ተጋላጭነት እንዳለባቸው የቬራኮድ (Veracode) ጥናት ይፋ ማድረጉን ይሄው የመረጃ መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ይነግረናል።

ይህ የተጋላጭነት መጠን ከሌሎች ሴክተሮች አንጻር በጣም ከፍተኛ የሚባል የሳይበር ጥቃት ተጋላጭነት መሆኑን በሳይበር ደህንነት ዘርፍ ላይ የተሰማራው "ቬራኮድ" ኩባንያ በጥናቱ መጠቆሙንም ይገልፃል። ከሌሎች ኢንዱስትሪዎች ጋር ሲነጻጸር ለመንግሥት አገልግሎት ሰጪ ሴክተሮች ጥቅም ላይ የዋሉ መተግበሪያዎች ላይ የተገኙ ክፍተቶችን ለመጠገን በእጥፍ የመጠገኛ ጊዜ እንደሚጠይቅ ነው ተመራማሪዎቹ ይፋ ያደረጉት።

ከዚህ ባሻገር 60 በመቶ የሚሆኑት የህዝብ ቤተ-መጽሐፍት ላይ የሚገኙ ክፍተቶች ሳይጠገኑ እስከ ሁለት አመት እንደሚቆዩም የተገለጸ ሲሆን፤ ይህ ጊዜም ከሌሎች ሴክተሮች አንጻር ሲታይ እጥፍ ጊዜያት እንደሚቆይ እና ከአጠቃላይ ሲታይ ደግሞ እስከ 15 ወራት የተራዘመ ጊዜ እንደሚጠይቅ ታውቋል። ይህን የጥናት ሪፖርት ሲዘጋጅ በህዝብ አገልግሎት መስጫ ፣ በማኑፋክቸሪንግ ፣ በፋይናንስ አገልግሎቶች ፣ በተለያዩ ምርቶች ችርቻሮ ላይ ባሉ ዘርፎች ፣ በሆቴል፣ በጤና አጠባበቅ እና በቴክኖሎጂ ክፍለ ኢኮኖሚ ውስጥ ተግባራዊ ከሆኑ ግማሽ ሚሊዮን መተግበሪያዎችን ከ20 ሚሊዮን በላይ መረጃዎች ላይ መንተራሱን ቬራኮድ ጠቁሟል።

የቬራኮድ ዋና የምርምር ኦፊሰር የሆኑት ክሪስ ኢንግ፣ በህዝብ አገልግሎት ዘርፍ ላይ በኃላፊነት ያሉ እና ፖሊሲ የሚያወጡ አካላት ጊዜያቸው ያለፈባቸው የቴክኖሎጂ ውጤቶች እና ከፍተኛ የህዝብ ሚስጥራዊ መረጃ የያዙ መተግበሪያዎች በመረጃ መዝባሪዎች ቀዳሚ ኢላማ መሆናቸውን ሊገነዘቡ እና የማስተካከያ ርምጃዎችን ሊወስዱ ይገባል ብለዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በተወካዮች ምክር ቤት በነበራቸው ቆይታም ከህዝብ እንደራሴዎች ለተነሳላቸው የሳይበር ደህንነት ስጋት ምላሽ የሰጡት የሚያመለክተው ጠንካራ የደህንነት መሰረተ ልማትና የመከላከል አቅም የማይገነባ ከሆነ አገሪቱ ልክ እንደቀሪው ዓለም ሁሉ "የሳይበር ደህንነት" ጉዳይ በእጅጉ እንደሚያሰጋት ነው።

# ወቅታዊ ትንታኔ

## «ኢትዮጵያ ታምርት» - በአገሪቱ ኢኮኖሚ አዎንታዊ ሚና እንዲኖረው

**አስቴር ኤልያስ**

‹‹ኢትዮጵያ ታምርት›› ንቅናቄ የአገር ውስጥ ችግሮችና ዓለም አቀፍ ጫናዎች የሚቋቋም ኢንዱስትሪ እስከ መፍጠር እንደሚዘልቅ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር መግለጹ ይታወቃል። ንቅናቄው የአንድ ወቅት የዘመቻ ሥራ ሆኖ እንዳይቀር ሊሠራባቸው የሚገቡ ነጥቦች መኖራቸውን ደግሞ በዘርፉ ያሉ ባለሙያ ይናገራሉ።

በኢትዮጵያ ታምርት መርህ ላይ አዲስ ዘመን ያነጋገራቸው፤ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በዲቨሎፕመንት ኢኮኖሚክስ ሶስተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ የሚገኙና በሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የልማት ምጣኔ ትምህርት ክፍል መምህር፣ ተመራማሪና እድገት በልማት ኢኮኖሚ ዙሪያ አማካሪ እጩ ዶክተር ዘካሪያስ ሚኖታ እንደሚናገሩት፤ በዓለም አቀፍ ደረጃ ማምረት በዋናነት ሶስት ዘርፎች አሉት። እነዚህም ማምረት፣ መሸመትና ማሰራጭት ናቸው።

ምርት ለሁሉም ነገር መነሻ ነው። ምርት ሳይኖር ስለፍጆታ ማውራት አይቻልም። እንዲሁም ማምረትና መሸመት ሳይኖር ስለስርጭት ማውራት አይቻልም። እነዚህ ሶስቱ ነገሮች በውስጣቸው በዋናነት አራት ነገሮችን ይይዛሉ። እነዚህም ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ተቋማዊና አካባቢያዊ ነገሮች ናቸው። በመሆኑም ኢትዮጵያ ታምርት የሚለው መርህ በአሉታም ሆነ በአዎንታ ጎኑ ሁሉንም ነገር በዚህ መልኩ የሚነካ ነው።

ወደ ማምረት ሲመጣ መሰረት የሚያደርገው አራት ነገርን ነው። ይኸውም የሰው ኃይል፣ መሬት፣ ካፒታልና ቴክኖሎጂ እንዲሁም እውቀት የሚባሉት ናቸው። በእነዚህ አራቱ ነገሮች የተሻለ ምርት ማግኘት እንደሚቻል የሚናገሩት እጩ ዶክተሩ፣ በተቃራኒው ሊሆን የሚችልበትም አጋጣሚ ይኖራል ይላሉ። ጥሩውንም መጥፎውንም ማድረግ የሚችለው ግን ራሱ የሰው ልጅ እንደሆነ ይገልጻሉ።

ለምሳሌ የሰው ሀብት የሚባለው ምርታማነት እንዲኖር ትልቁን ድርሻ የሚወጣ ነው። ይህ ለሁሉም ማለትም ለቴክኖሎጂው፣ ለካፒታሉም ሆነ ለመሬቱም መነሻ ነው። ስለዚህም የሰው ዝግጁነት የአንበሳውን ድርሻ የሚይዝ ነው። ምክንያቱ ደግሞ የሰው ልጅ ሁሉንም የሚያቀናጅ በመሆኑ ነው። ካፒታሉም መሬቱም ሆነ ቴክኖሎጂውን የሚያቀናጀው ራሱ የሰው ሀብት የሚባለው ነው።

እርሳቸው በተጨማሪነት ሌላ አንድ ጽንሰ ሐሳብ ሲጠቅሱ እንዳሉት፤ ምርት ሲኖር በአካባቢው የራሱ የሆነ ጫና ይፈጥራል። የኢኮኖሚ እንቅስቃሴና አካባቢ አንዱ ሌላውን ይቃረናል። ለምሳሌ ተፈጥሮ በሆኑ ነገሮች ላይ መሰረት ያደረጉ አገሮች ከአካባቢያቸው ጋር እየተጣሉ ነው ማለት ነው። በአካባቢው ላይ የሚያመጣው ተጽዕኖ በጣም ከባድ ነው። ይህም ተጽዕኖ የአየር ጸባይ መዛባት፣ ዝናብ በወቅቱ አለመዝነብ፣ ሙቀትና መሰል ነገር ሲሆን፣ ይህ ነገር ከሰው ልጅ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ጋር ተያይዞ የሚመጣ ነው።

በዓለም ላይ የሚስተዋለው 99 በመቶ የአየር ቀውስ እየተፈጠረ ያለው በሰው ልጆች እንቅስቃሴ ነው። ይህም የማምረት፣ የመሸመትና የማሰራጨት እንቅስቃሴ የሚባለው ነው። በተፈጥሮ በኩል የሚመጣው ተጽዕኖ ግን አንድ በመቶ ብቻ ነው። ለምሳሌ የእሳተ ጎመራ ሂደት ለውጡን ማየት የሚቻለው በሺዎች በሚቆጠሩ ዓመታት ውስጥ ነው። ይህም በጣም ዘገምተኛ የሆነና ብዙ ጊዜ የሚቆይ ሲሆን፣ በተፈጥሮ በኩል ይመጣሉ የሚባሉት ነገሮች የሚያመጡት ተጽዕኖ አንድ በመቶ ብቻ ነው ማለት ነው። ስለዚህም በዓለም ላይ የሚፈጠረው የአየር ቀውስ ምክንያት የሰው ልጅ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ነው ማለት ነው።

ስለዚህ ምርት ስናመርት እነዚህን ነገሮች ታሳቢ ማድረግ የግድ የሚል እንደሆነ ነው እጩ ዶክተር ዘካሪያስ የጠቀሱት። ከዚህ ቀደም ብዙ ትኩረት ባንሰጥም እንኳ የተፈጥሮ ሀብቱ፣ ደኑ፣ ውሃው በጣም ብዙ ስለሆነ ከስርጭት አኳያ ስላልተጎዳ የመቋቋም ጉልበት ነበረው። አሁን የሰው ልጅ ቁጥር እየጨመረና መሬቱም ከህዝብ ቁጥር አንጻር እየቀነሰ ስለመጣ ለአየር ቀውስ የመጋለጥ እድሉ እየሰፋ መጥቷል። በአብዛኛው ታዳጊ አገሮች ላይ

> **ኢትዮጵያ ታምርት ሲባል በአካባቢው ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ተገቢ ጥንቃቄ የታከለበት ሲሆን ይገባል። እንዲሁም የተቋማት ዝግጁነትን ታሳቢ ያደረገ ብሎም የአካባቢዎችን አግሮኢኮሎጂ መሰረት ያደረገ መሆንም ይጠበቅበታል**

ለአገልግሎት የሚውለው ከተፈጥሮ የሚገኘው ሀብት ነው። ለምሳሌ ልብስ፣ እቃም ሆነ ሌሎችም ግብዓቶች የሚገኙት ከአካባቢያችን ካሉ ተፈጥሮዎች እንደሆነ ይገልጻሉ።

ስለዚህ ኢትዮጵያ ታምርት ሲባል በአካባቢው ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ተገቢ ጥንቃቄ የታከለበት ሊሆን ይገባል። እንዲሁም የተቋማት ዝግጁነትን ታሳቢ ያደረገ ብሎም የአካባቢዎችን አግሮኢኮሎጂ መሰረት ያደረገ መሆንም ይጠበቅበታል። ለምሳሌ አንድ ቦታ ላይ ስንዴ የሚመረት ከሆነ ሁሉም ቦታ ላይ ስንዴ ይመረታል ማለት አይደለም። ሌላ ቦታ የሚመረተው ሩዝ ወይም በቆሎ ወይም ደግሞ አትክልትና ፍራፍሬ ሊሆን ይችላል። መቃኘት ያለበት እንደየአግሮኢኮሎጂው ነው።

ወደ ኢንዱስትሪውም ሲኬድ ደግሞ ለምሳሌ አንድ ቦታ ላይ ለሲሚንቶ ምርት የሚሆን ግብዓት በብዛት ያለበት አካባቢ ከሆነ ማምረት የሚገባው ራሱ ሲሚንቶን ነው። ሌሎች ፋብሪካዎችን ከመገንባት ይልቅ የሲሚንቶ ፋብሪካዎችን ማስፋፋቱ ተመራጭ ይሆናል።

በዋናነት የምርት ዋጋም ሆነ ስርጭት የሚወሰነው ያንን በማምረት የሚወጣ ወጪ ከግምት ውስጥ ሲገባ ነው። የሚወጣው ወጪ ከፍተኛ ከሆነ የምርት አቅርቦትም ሆነ ስርጭት ሊሳለጥ አይችልም። አሊያም ውድ ይሆናል። የቱንም ያህል የመግዛት አቅም ቢኖር እንኳ ትክክለኛ ዋጋ ካልሆነ በስተቀር ውድ ከሆነ ሰው አይፈልገውም። ስለሆነም ምርት ሲመረት በዋናነት ግብዓትንም ቴክኖሎጂንም መሰረት ያደረገና በተመጣጣኝ ዋጋ መሆን አለበት። በዝቅተኛ ዋጋ ማምረትና አገልግሎት መስጠት የሚቻልበት ሁኔታ መፈጠር አለበት። ስለሆነም ኢትዮጵያ ታምርት ሲባል አንደኛ በዝቅተኛ ወጪ መሆን አለበት ይላሉ።

እርሳቸው እንደሚናገሩት፤ ኢትዮጵያ ታምርት ሲባል ሌላው ነገር አግሮኢኮሎጂውን፣ ተደራሽነትንና ዝቅተኛ ዋጋን ታሳቢ ማድረግም ያስፈልጋል። በአንድ ቦታ ያለ ኢንዱስትሪ የሚያመርተውን ምርት ለሌሎች አካባቢዎች ማድረስ ካልተቻለ አቅርቦት ላይ ችግር ሊፈጠር ይችላል። ስለዚህ ትርፍ እንዲኖር አድርጎ ማምረት ደግሞ ይጠበቃል። ትርፍ ማምረት ካልተቻለ ውጤታማ ወይም ቀጣይነት ያለው እንቅስቃሴ ሊኖር አይችልም። ትርፍ ሲኖር ለነገ የሚሆን ግብዓት ማዘጋጀት ይቻላል።

ለትርፋማነት ግብዓት የሚሆኑ ተቋማትን መገንባት ደግሞ ያስችላል። በተለይም በእውቀት፣ በልምድ፣ በቴክኖሎጂ ከአገር ውስጥ ገበያ ተነስቶ እስከ ዓለም አቀፍ ገበያ ድረስ ትስስሩን ማጠናከር የሚቻለው ትርፍ ማምረት ሲቻል ነው። ትርፍ ካልተመረተ ከእጅ ወደአፍ ይሆናል ይላሉ።

ኢትዮጵያ ታምርት ሲባል በተመሳሳይ ቴክኖሎጂም መታሰብ አለበት። ይህ ደግሞ ለምሳሌ በግብርናው ዘርፍም ሆነ በሌላው አገር በቀል ቴክኖሎጂን በመጠቀም ሊሆን ይችላል። ቴክኖሎጂ ሲባል ማንኛውኛም ምርትን ሊያሳድግ የሚችል ከሐሳብ ጀምሮ ያለ ዘዴ ሊሆን ይችላል። ቴክኖሎጂው ምርት መሰብሰብ ላይም ሆነ ስርጭት ላይም ሊሆን ይችላል። ምክንያቱም በአሁኑ ጊዜ ከቴክኖሎጂ ተላቅቆ ምርት ማምረት አይቻልም። ይሁንና ቴክኖሎጂው በሁሉም ቦታ መድረስ ያለበት ዝቅተኛ በሆነ ዋጋ ነውና እዚህ ላይ በአግባቡ ማሰብ ይጠይቃል።

ሌላው እነዚህን ሁሉ ሊያስተባብር የሚችል ተቋማዊ አደረጃጀትና ተቋማዊ ስርዓት ሊኖር ይገባል። እንዲህም ሲባል ልማቱን ለማሳለጥ የሚወጡ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ መመሪያዎች፣ ደንቦች፣ አሰራሮችና ፕሮጀክቶች ሲሆኑ፣ እነዚህ ሁሉ ምርትን ለማሳደግም ሆነ ምርትን ለማቀጨጭ ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ ናቸው። ስለሆነም የሚወጡ አሰራሮች ምን ያህል ሊያሰሩ እንደሚችሉ መታወቅ አለበት። ለምሳሌ ኢትዮጵያ ታምርት ሲባል አካባቢውን ታሳቢ ያደረገ መሆን አለበት።

ከኢትዮጵያ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ጋር ቅንጅት በመፍጠር ሊሰራ ይገባል። ይህ ደግሞ በአንድ ሰሞን ዘመቻ ሳይሆን መደበኛ በሆነ መልኩ ታሳቢ ተደርጎ በእቅድ መሰራት አለበት። አካባቢ ሳይበከል ምርት ማምረት የሚያስችለን መንገድ መጠቀም ተገቢ ነውና ተቋማዊ አደረጃጀት ወሳኝ ነው።

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተገኝተው ከምክር ቤቱ አባላት ለተነሱት ጥያቄዎች ማብራሪያና ምላሽ በሰጡበት ወቅት ኢንዱስትሪን አስመልክተው እንደተናገሩት፤ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ‹‹ኢትዮጵያ ታምርት›› የሚባል በጣም ጥሩ ጅማሮ ጀምሯል። ዋና አላማው አጠቃላይ ያሉ ኢንዱስትሪዎች ቢያንስ 50 ከመቶ ማምረት እንዲችሉ ነው። ይህ ጅማሮ ጥሩ ውጤትም እያመጣ ነውና፤ ተጠናክሮ ይቀጥላል።

ይህ ብቻ ሳይሆን ከለውጥ በፊት ኢትዮጵያ ሶስት የኢንዱስትሪ ፓርኮች ነበሯት ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ እነሱም ሃዋሳ፣ ኮምቦልቻና መቀሌ መሆናቸውን አስታውሰዋል። ኢትዮጵያ ከለውጡ በኋላ አስራ ሁለት የገነባች ሲሆን፣ ሶስት የአግሮ እና ዘጠኝ የኢንዱስትሪ ፓርኮች እንደሆኑም ተናግረዋል።

እንደ እርሳቸው ገለጻ፤ በየትኛውም መመዘኛና በየትኛውም ቁጥር በኢንዱስትሪ፣ በትምህርትም፣ በስኳርም፣ በቴሌም፣ በአየር መንገድም፣ እንዲሁም በመብራትና በውሃም ሊወዳደር አይችልም። አስደማሚ እምርታዎች አሉ። የሚለፉና የሚተጉ ኢትዮጵያውያን በየቦታው አሉ። ነገር ግን በዛው ልክ የሚሰርቅ፣ የሚያላግጥ ወሬ የሚተነትንና መፍትሄ የማያመጣ ስላለ ከዚያ በላይ መሄድ ሲገባ የቀነሰ ነገር ይኖራል።

የኢንዱስትሪ ሚኒስትሩ አቶ መላኩ አለበል ከኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ጋር በነበራቸው ቆይታ በአገር ውስጥና በውጭ ጫናዎች እየተፈተነ ያለውን ኢንዱስትሪ መታደግ የሚያስፈልግበት ነባራዊ ሁኔታ መምጣቱ ተናግረዋል። በጦርነትና በተከሰተው በኮቪድ 19 ወረርሺኝ ሳቢያ በርካታ ኢንዱስትሪዎች ስራቸውን አቁመዋል፤ ቀሪዎቹም ማምረት ከሚገባቸው ከ50 በመቶ በታች እያመረቱ እንደሆነም አስረድተዋል።

በተለያዩ የአለም አገራት የሚደረጉ ግጭቶች ወደ ውጭ በሚላኩና ከውጭ በሚገቡ ምርቶች ላይ ጫና በማሳደሩ ኢትዮጵያንና መሰል በማደግ ላይ ያሉ አገራት ኢኮኖሚ በከፍተኛ ሁኔታ እየጎዳው እንደሆነ እንደ ማሳያ ሊወሰድ ይችላል ብለዋል። ኢትዮጵያ በእነዚህና በሌሎች የተለያዩ ችግሮች ሳቢያ የተጎዳውን ኢንዱስትሪ በዘላቂነት ለማቋቋም ‹‹ኢትዮጵያ ታምርት›› የሚል ንቅናቄ መጀመሯን አስታውሰዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ኢንዱስትሪ ላይ የሃይል፣ የፋይናንስ፣ ሎጀስቲክስና ቢሮክራሲ ችግር ቢፈታ እና ከ50 በመቶ በላይ ቢያድግ ምርታችን በርግጠኝነት በከፍተኛ ደረጃ ለውጥ ያመጣል ይላሉ። ኢንዱስትሪ ውስጥ ሁለት ነገር ማየት ይገባል። አንደኛ አግዋ ቀርቶ እንኳ እያለ ዘንድሮ የኤክስፖርት ንግድ አድጓል። አጎዋም ተዘግቶ ጫናም እያለ የኤክስፖርት ምርት አድጓል እንጂ አልቀነሰም ሲሉም ያክላሉ። ይህ ብቻ ሳይሆን የገቢ ምርት መተካት ላይም ከፍተኛ ስራ መሰራቱን ተናግረዋል። ቀደም ሲል በቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ የሚወጣባቸው የከሰል ድንጋይ፣ ገብስ፣ ልብስ፣ ጫማ፣ የደምብ ልብስና ሌሎችም በሀገር ውስጥ እየተመረቱ መሆኑን ነው ያመለከቱት።

እጩ ዶክተር ዘካሪያ በበኩላቸው፤ እነዚህን ጉዳዮች ታሳቢ ያደረገ ስራ መስራት ተገቢነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ መርሁ ግን የአንድ ወቅት የዘመቻ ስራ ሆኖ እንዳይቀር ሊሰራበት ያስፈልጋል ሲሉ ጠቅሰዋል። የአንድ ሰሞን ዘመቻ ከሆነ ግን የሚፈጠረው ብክነት ነው። ሰዎች ከዚህ በኋላ የሚመጡ መርሃ ግብሮችን አዎንታዊ በሆነ መልኩ እንዳይቀበሉ ሊያደርግ እንደሚችል ስጋታቸውን ተናግረዋል።

ስለዚህ በመጀመሪያውኑ በአግባቡ ተጠንቶ እንዲሁም አደረጃጀት ተፈጥሮለት በተጨማሪም ተጠያቂነት ተፈጥሮለት ብሎም በተዋረድ ግንዛቤው እንዲፈጠር ተደርጎለት መሰራት አለበት። ሌላው ቀርቶ ኢንዱስትሪው ያለበት አካባቢ ያለ ማህበረሰብ ኢንዱስትሪው ስለሚያመርተው ምርትና ስለሁኔታው ተገቢው እውቀት ሊኖረው እንዲገባ ማድረግም የግድ ነው። ዝም ተብሎ ሄዶ የአንዱን አካባቢ መቆፈር ተገቢ ካለመሆኑም በተጨማሪ አካሄዱም አደገኛ ነው። ህዝቡ በአካባቢው ስለሚሰራው ስራ ማወቅና ሊጠብቀው የሚችልም መሆን ይኖርበታል። ህዝብ ያላወቀው ነገር ጥፋቱ የከፋ ነው። ምክንያቱም ቀጣይነቱ ላይ ኢንዱስትሪው ፈተና ሊጋረጥበት ይችላልና ህዝቡን ማሳተፍ መልካም ነው። ያ ሲሆን፣ ህዝቡ የባለቤትነት ስሜት እንዲኖረው ያደርገዋል፤ ንብረቱንም እንደራሱ ንብረት መጠበቅ ይጀምራል። ከዚህም ባሻገር ኢንዱስትሪው ያለበት አካባቢ ያለ የህብረተሰብ ክፍል ከኢንዱስትሪው ተጠቃሚ ሊሆንም ይገባል ብለዋል።

ሌላው ይላሉ እጩ ዶክተሩ፣ በኢትዮጵያ በየጊዜው የሚታየው የተቋማት መለዋወጥ በዚህ መርህ ላይ ጫና የሚያሳድር ነውና እዚህ ላይ ጥንቃቄ ማድረጉ ተገቢ ነው። ተቋማትን ማዋሃድና ማፍረስ መረጃም እንዲጠፋ ከሚያደርገው ነገር አንዱ ሲሆን፣ ሰራተኛውም ጥርጣሬ ውስጥ ይገባል፤ የተቋማት መቀያየር በኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ላይ የሚያሳድረው ጫና በቀላሉ መታየት የለበትም። ስትራቴጂ ሲቀየር ከጊዜ፣ ከገንዘብና ከጉልበት አኳያ ያለው ተጽዕኖ በጣም ከባድ ነው።

እነዚህ የተጠቀሱት ዋና ዋና ጉዳዮች ተሟልተው የሚተገበሩ ከሆነ ኢትዮጵያ ታምርት የሚለው መርህ በአግባቡ ተግባራዊ ሊደረግ ይችላልና በአገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ የበኩሉን አዎንታዊ ሚና ይጫወታል። አንዱ የስራ እድል መፍጠሩ ነው። የስራ እድል ተገኘ ማለት ሰው ገቢ አገኘ ማለት ነው፤ ገቢ ሲያገኝ የመግዛት ፍላጎት ይፈጠራል። እግረ መንገዱን ይቆጥባል፤ መቆጠብ ማለት ደግሞ ሌላው ኢንቨስትመንት እንደማለት ነው። ከዚህ ጎን ለጎን አምራቹ በመሸጥ የሚያገኘው ገቢ ይኖረዋል። ለመንግስት ደግሞ ከምርት የሚገኝ ግብር ይኖራል።

የምጣኔ ሀብት ባለሙያው እንደሚናገሩት፤ ከኢኮኖሚ ጠቀሜታው በተጨማሪ ሌላ ጥቅም አለው። ከፖለቲካው በኩልም ሲታይ እንዲሁም የማህበራዊ ሁኔታው ተረጋግቶ እንዲሄድ ከማድረግ አኳያም የራሱ የሆነ በጎ ተጽዕኖ አለው ብለዋል። ከዚህ በተጨማሪ ስልጡን ህዝብ እንዲኖር ያደርጋል። ልምድና እውቀት በቀላሉ ያለምንም ወጪ ማግኘት ያስችላል። በጥቅሉ የቴክኖሎጂ ሽግግርን በቀላሉ ያስገኛልና ፋይዳው ብዙ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

ንቅናቄው በ2022 ዓ.ም እንደ አገር የበለጸገች ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ የተያዘውን ዕቅድ ለመተግበር ሰፊ እድል እንደሚኖረው ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የተገኘው መረጃ ያመለክታል። አገሪቱ ያላትን የተፈጥሮ ሀብት በመጠቀም በቀጣዮቹ አስር ዓመታት ኢንዱስትሪው አገራዊ የምርት ድርሻው ከ6 ነጥብ 9 በመቶ ወደ 17 ነጥብ 2 በመቶ ለማሳደግ ግብ መጣሉም ታውቋል።

የኢንዱስትሪ ሚኒስትሩ እንደተናገሩት፤ አገሪቱ በ2022 ዓ.ም ከአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፉ በዓመት ወደ ውጪ ከሚላክ ምርት አሁን ከሚገኘው 4 መቶ ሚሊዮን ዶላር ወደ 9 ቢሊዮን ዶላር ማሳደግ ዋነኛ ዓላማውም ነው። የአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ የማምረት አቅም ወደ 85 በመቶ ማሳደግ እንዲሁም ከ5 ሚሊዮን ለሚልቁ ዜጎች የስራ እድል ለመፍጠር ተወጥኗል።

የኢንዱስትሪዎችን የማምረት አቅም ለመጨመር የሀይል አቅርቦት፣ የመሬት፣ የሥልጠና፣ የብድር አቅርቦትና ተያያዥ ችግሮችን ለመፍታት ከባለድርሻ አካላት ጋር ከመቼውም ጊዜ በላይ እየተሰራ መሆኑንም ሚኒስትሩ አስረድተዋል።

ማህበራዊ

# ሴቶች

# የጊዜ አጠቃቀም ኑሮን ያቀለለ ህይወትን ይቀይራል

**ሰላማዊት ውቤ**

ቢሮ የሚውሉ ሴቶች ከወንድ ሠራተኞች የሚለዩባቸው ብዙ ኃላፊነቶች አሉባቸው። በቤት ውስጥ ያለባቸውን ድርብ ኃላፊነት እንደ አንድ ማሳያ መጥቀስ ይቻላል። ጎልቶም ባይወጣ በእነዚህ ድርብ ኃላፊነቶች ምክንያት አንዳንድ ሴቶች ሲቸገሩ ይስተዋላል ። ሁለቱንም ሃላፊነቶች አስታርቆ መሄድ የሚሳናቸው ጊዜም ብዙ ነው። አንዳንዴ ከኃላፊነቱ መብዛትና ከጫናው መበርታት የተነሳ ከባድ የሆነ የህይወት ውጣ ውረድ ወስጥ የሚገቡበትም ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል ። በዚህ ምክንያት ብዙ ጊዜያቸው ወደቤታቸው ይሆንና የመማር ራሳቸውን በእውቀት የማሳደግና ከሰዎች የመወዳደር ሁኔታው አጣብቅኝ ውሰጥ ይገባል። በሌላ በኩልም በተሰማሩበት የስራ መስክ ላይ ከሌሎች በተለይም ከወንዶች እኩል ተወዳድረው በቅተው የመውጣት ሁኔታቸው ላይ ከፍተኛ የሆነ ጥላን ያጠላልም፡፡ በተለይ ሥራ ገበታ ላይ ከተሰማሩ በኋላ በዚሁ ድርብ ኃላፊነት ምክንያት ሥራቸውን በሰዓቱና በአግባቡ ላይሰሩም ይችላሉ።

ለዛሬ የቢሮና የቤት ውስጥ ኃላፊነቶችን አስታርቆ በመሄድ ረገድ ሰዓት አጠቃቀምን ማወቅና እንደ ልምድ እያዳበሩ መምጣት ወሳኝ የመሆኑን ተሞክሩ ከወይዘሮ አልማዝ ለማ እናያለን ፤ ወይዘሮ አልማዝ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የእንስሳት የተፈጥሮ ቅርስ መዘክር (ሙዚየም) ኃላፊ ሆነው እያገለገሉ ይገኛሉ።

ወይዘሮዋ የሥራ ቦታቸው አራት ኪሎ ሲሆን የመኖርያ አድራሻቸው ደግሞ ከአዲስ አበባ ከተማ 30 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በምትገኘው ሰበታ ከተማ ነው ። ‹‹ትልቁ የጊዜ አጠቃቀምን ማወቅ መቻል ነው›› የሚሉት ወይዘሮ አልማዝ የስራ ቦታቸው የሚገኝበት አካባቢ ከማለዳው 12 ሰዓት እንደሚደርሱም ይናገራሉ። ከንጋቱ 11 ሰዓት ከመኝታቸው ተነስተው አስፈላጊውን ነገር ካከናወኑ በኋላ ከቤታቸው ከጠዋቱ 12 ሰዓት በመውጣትና ትራንስፖርት በመያዝ በቶሎ የስራ ገበታቸው ላይ እንደሚገኙም ይናገራሉ፡፡

“ከሰፈሬ ተነስቶ አራት ኪሎ የሚዘልቅ ፐብሊክ ሰርቪስ አለ፤ ነገር ግን የመነሻው ሰዓት ትንሽ ዘግየት ስለሚልና ያስረፍደኝ ይሆናል ብዬ ስለማስብ አልጠቀምበትም ፤ ከዛ ይልቅ በትራንስፖርት እመጣለሁ ምናልባት በሰርቪሱ ብመጣ የማተርፈው ገንዘብ ይኖር ይሆናል ነገር ግን እኔ ከገንዘብ ይልቅ ጊዜያን ማትረፍ ስለምፈልግ በታክሲ እጠቀማለሁ” ይላሉ፡፡

ቢሯቸው ከደረሱ በኋላም ቦርሳቸውን በማስቀመጥ ባተረፉት ሰዓት የዕለት ተግባራቶቻቸውን ማከናወናቸውን ይቀጥላሉ። መሄድ ካለባቸው ወደ ቤተእምነት በመሄድ ቀጣይ ተግባራቸው ደግሞ ስፖርት ቤት (ጅም ) መግባት ነው ። እዚህ ቢያንስ እስከ 40 ደቂቃ ያሳልፋሉ። ከጅም መልስ ለ20 ደቂቃ ሻወር ከወሰዱ በኋላ ይወስዳሉ። ከአንድ ሰዓት ከ20 በኋላ ቢሯቸው ይገባሉ። በማህበራዊ ሚዲያ ላይ ጊዚያቸውን ማጥፋት ስለማይፈልጉ ቀጥታ ከሥራ ጉዳዮች ጋር ተያይዞ የሚጠቀሙበትን ኢሜል ላፍታ መልከት ያደርጋሉ። ከጠዋቱ አንድ ሰዓት ተኩል ጀምሮ እስከ 11 ሰዓት ከ 30 ወይዘሮ አልማዝ መደበኛ ሥራቸውን ትኩረት አድርገው የሚሰሩበት ወቅት ነው። ምሳ ይዘው ስለሚመጡ ሻይም እዛው ቢሯቸው አፍልተው ስለሚጠጡ ለሻይ ቡና ብለው የሚያባክኑት ጊዜም የለም ይህ ደግሞ በስራቸው ውጤታማ እንዲሁኑ አስችሏቸዋል።

እሳቸውም ሆኑ የሥራ ባልደረቦቻቸው እንደሚሉት ሥራው የሚሰራው ከእሁድ እስከ እሁድ በመሆኑ ምንም እረፍት የለም። ሠራተኞቹ ቅዳሜና እሁድ ብቻ ሳይሆን በበዓላት ወቅቶች በሙሉ ቢሮ መግባት ይጠበቅባቸዋል። ከሁለት



ፎቶ በአዮብ ተፈራ

ወንዶች በስተቀር ቀሪዎቹ በሥራቸው ያሉት የሙዚየሙ ሰራተኞች ሴቶች ናቸው። ከእሁድ እስከ እሁድ ሥራ ገበታቸው ላይ ከመገኘት ባሻገር በየቤታቸው ውስጥም የሚጠብቃቸው ድርብ ሃላፊነት አለ። ወይዘሮ አልማዝ ሰለቸኝ ደከመኝ ሳይሉ እነዚህን ክፍተቶች በመሸፈን ቀዳሚ ናቸው። በአብዛኛው ቅዳሜ የሚገቡ ባይሆንም የአስጎብኝንና ጨምሮ እስከ ጥበቃ ድረስ ያለውን ሥራ ኃላፊ ነኝ እኔን አይመለከትም ብለው ሳይገፉ ገብተው በመሥራት ይሸፍናሉ።

እንደ አለቃ ቢያስተባብሩም የሥራ ቅርበታቸው የአለቃና ምንዝር ሳይሆን የጓደኛ ዓይነት መሆኑ ለመሸፋፈኑ ጠቅሟቸዋል። ሥራው በባህርይው በአንድ ሰው ብቻ የሚሸፈን አለመሆኑ ተባብሮ ለመስራትም አግዟቸዋል። ምክራቸውን ትንሽና ታናሽ ናት ብለው ሳይተው ይቀበላሉ። ደረጃቸውንና ማንነታቸውን ያከብሩላቸዋል። ህፃናትም ሆነ አዋቂና የውጪ ዜጋ ጎብኚ የእንስሳት የተፈጥሮ ቅርስ መዘክርን አስመልክቶ ግንዛቤ መጨበጥ ይፈልጋል። ሙዚየሙም የተቋቋመው ለዚህ ነውና አስጎብኚዎች በማይኖሩበት ጊዜ እየተዟዟሩ ገለፃ ሲያደርጉና ሲያስተምሩ ብዙ እንቅስቃሴ ያደርጋሉ። በሙዚየሙ ያሉት ሦስት ዓይነት የወፍ ዝርያዎች በራሳቸው ብዙውን የትምህርት ጊዜ ይወስዳሉ። ለምሳሌ ከነዚህ አንዷና መሬት ወርዳ ጥራጥሬ በመልቀም ምትመገበዋን ወፍ እንዳነሷት እነዚህ የወፍ ዝርያዎች ማስቲካዋ ጥሬ ትመስላቸውና ያነሷታል። ማስቲካ ደግሞ በተፈጥሮው የራሱ የማጣበቅ ባህርይ ስላለው መንቁራቸው ላይ ይጣበቃል። በዚህ ምክንያት በረሃብና በውሃ ጥም ይሞታሉ። በመሆኑም ያኘክነውን ማስቲካ በወረቀት ወይ በሶፍት ጠቅልለን ማስወገድ እንደሚገባ ለጎብኝዎች ለማስተማር ከገለፃ ጋር ብዙ እንቅስቃሴ ያደርጋሉ።

ማታ ከሥራ መልስ እቤታቸው ሲገቡ ብዙ ኃላፊነቶች ይጠብቋቸዋል ። በአሁኑ ወቅት ልጆቻቸውን በማሳደግ የቤትና የሥራ ጫናቸውን ስታቀልላቸው የነበረችው ሰራተኛቸው አብራቸው አለመሆኗ የቤቱን ኃላፊነት አክብዶባቸዋል።ከሥራ መልስ እሷ ታከናውናቸው የነበረውን የቤት ሥራዎች በሙሉ ይሰራሉ። አጋጣሚ ሆኖ ባለቤታቸው አብዝተው መስክ የሚወጡ በመሆናቸውና በቤት ውስጥ ባለመገኘታቸው ሁለቱን ልጆቻቸውን ማስጠናትና የቤት ሥራ ማሰራቱ ሰርክ የእሳቸው ኃላፊነት ነው። ማታ ላይ የጠዋት ልብሳቸውን ያዘጋጁና ማልደውም ትምህርት ቤት ይዘው የሚሄዱትን ምግባቸውን ይቋጥራሉ። ወይዘሮ አልማዝ በሚኖሩበት አካባቢም ያለውን ማህበራዊ ኑሮ ዕድር፣ ለቅሶ፣ የዓውድ ዓመትና ሌሎች ጉዳዮችን የሚያስተናግዱት ከሰኞ እስከ ቅዳሜ ባለው በዚህ ሰዓታቸው መካከል ነው። በተለይ ቅዳሜ ላይ ልጆቻቸውን ትምህርት ቤት ለመሸኘት የሚያደርጉት ሥራ ስለሚቀንስላቸው ሰዓቱን ለማህበራዊ ሕይወት ያውሉታል።

ወይዘሮ አልማዝ ጋር ቤተሰብ፣ ወዳጅ፣ ዘመድም በዚህ ሰዓትና በዓመት ዕረፍት ወቅት ነው የሚጠየቀው።ይሄን መሰሉን ሰዓት አጠቃቀማቸውን ከልጅነታቸው ጀምሮ ከወላጆቻቸው በመውረስ እያዳበሩት እንደመጡ ይናገራሉ። ለወላጆቻቸው አራተኛ ልጅ ሲሆኑ እሳቸውን ጨምሮ ሦስት ወንድና ሦስት ሴት ልጆች ያላቸው ቢሆኑም በቤታቸው የወንድና የሴት የሚባል የሥራ ክፍፍል እንዳልነበረ ያስታውሳሉ። በተጨማሪም ሴት ልጅ የመጀመርያ ልጅ በመሆኗና ሴት ልጅን በሥራ የመጥመድ የማህበረሰብ አስተሳሰብ ጫና ድነዋል። የወንድና ሴት የሚባል የሥራ ክፍፍል ባለመኖሩ የወላጆቻቸው የበኩር ልጅ የሆነው ወንድማቸው እንጀራ ከመጋገር ጀምሮ የቤት ውስጥ ሥራን በሙሉ እየሰራ እንዲያድግ ነው የተደረገው። ታላቅ ወንድማቸው እሳቸውን ጨምሮ ታናናሾቹን በማሳደጉ ረገድ ቤተሰቡን ይረዳ ነበር። በቤት ጽዳትና በልብስ አጠባም በኩል የሚተካላቸው አልነበረም። ሁለቱ ወንድሞቻቸው የቤቱ ታላቅ ስለነበሩ እነሱ ነበሩ የቤት ውስጥ ኃላፊነቱን በሙሉ የሚወስዱት ።

‹‹የትምህርት ዕድል አግኝቶ ያደገ ባለመሆኑ የአባቴ ገቢ ምንጭ ትንሽ ነበር›› የሚሉት ወይዘሮ አልማዝ አባታቸው ጡረታ ከወጡ በኃላ በአነስተኛ እርሻ ሥራና ከብቶች በማርባት ተሰማርተው የነበሩ መሆናቸውንም ያነሳሉ። እንዳከሉት እናታቸው በፊናቸው ባለቤታቸውን የገቢ ምንጫቸውን በሚያጎለብቱበት አንፃር አብዝተው ሲያግዟቸው ነው የኖሩት። ለአብነት እናታቸው አንድ ሳይሆን ሁለት ሶስት የገቢ ማስገኛ ንግዶች ላይ ተሰማርተው መሥራታቸው ይጠቅሳሉ። የሸቀጣ ሸቀጥ መደብር ፣ ሻይ ቤት፣ ወፍጮ ቤት እናታቸው ገቢያቸውን ከፍ በማድረግ ባለቤታቸውን ለማገዝና ቤተሰባቸውን በተገቢው መንገድ ለማስተዳደር ሲሰሩባቸው የነበሩ ሥራዎች ናቸው።

ሴቶቹ ከተወለዱ በኋላ ሦስተኛዋ ልጅና ታላቅ እህታቸው የቤት ውስጥ ሥራን እሳቸው ደግሞ የውጪ የውጪውን ሥራ አብዝተው ይወዱ እንደነበር ያስታውሳሉ። እህታቸው ለሻይ ቤቱ ዳቦ ሲጋግሩ እሳቸው ወፍጮ ቤት የመሄድና ዱቄት የማስፈጨት ፣ ሻይ ቤት ሄደው ዳቦና ሻዩን ሲሸጡ የመዋል፣ ወፍጮ ቤት ገንዘብ የመሰብሰብ ሥራ ይሰራሉ።

እንዲህም ሆኖ ወላጆቻቸው ሁሉም ልጆቻቸው በሥራ ጫና ከትምህርት እንዲደነቃቀፉባቸው ወይም እንዲደክሙባቸው አይፈልጉምና ለትምህርታቸውም ጊዜ እንዲሰጡ በወላጆቻቸው ይገደዱና ይደገፉም ነበር። በተለይ አባታቸው ዝቅተኛ ገቢና የኑሮ ደረጃ ላይ ለመኖር የበቁት ባለመማራቸው በመሆኑ የእሳቸው ዕጣ እንዳይደርሳቸው ለትምህርታቸው ከፍተኛ ትኩረት እንዲሰጡ ከጎናቸው ሆነው በእጅጉ ይደግፏቸው ነበር።

በቤት ውስጥ የሚሰጣቸው ሥራ ከትምህርት ገበታቸው እንዳያስተጓጉላቸው ከነበሯቸው ከብቶች ጋር የተያያዘውን የሌሊቱን ሥራ ከሌሊቱ ስድስትና ሰባት ሰዓት ተነስተው አባታቸው ይሰሩ እንደነበር ይናገራሉ ። እናታቸው በፊናቸው ከማለዳው 11 ሰዓት ይነሱና ከብቶች የበሉበትን ግርግም የማንሳትና የማፅዳቱን ሥራ ይሰራሉ። እንዲሁም ወተት ያልባሉ። ከዚያም ቁርስ አዘጋጅተው በማብላት ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት ይሸኛሉ። ከትምህርት ቤት መልስ ደግሞ እነሱ ለከብቶች የሚያስፈልገውን ያቀርባሉ ። ወፍጮ ቤት መሄድና ሌሎች የመላላክና እንደ ልብስና የተበላበትን ዕቃ ማጠብ ያሉ የቤት ውስጥ ሥራዎች ካሉ እስከ ማታ ድረስ ሲሰሩ ያመሻሉ ። የማታው ጊዜ በሙሉ ለልጆች ይሰጥና ይሸፍናሉ።ይሄ ሰዓት አጠቃቀምን ማዕከል ያደረገ የሥራ ባህልና ልምድ የባከነ ጊዜ ሳይኖራቸው ከትምህርት ቤት ወደ ሥራ ያሸጋገራቸው መሆኑንም ወይዘሮ አልማዝ ያወሳሉ።

ከሀሁ ዳዊት እስከ መድገም በመዝለቅ ትምህርት ከቄስ መጀመራቸውን የሚናገሩት ወይዘሮ አልማዝ ከአንደኛ እስከ ሦስተኛ ክፍል ያለውን የመጀመርያ ደረጃ ትምህርታቸውን ጌቴሴማኔ የሴቶች ገዳም ነው የተማሩት። ከስድስት እስከ ስምንት ሙሉጌታ ገድሉ የመጀመርያ ደረጃ ትምህርት ቤት ከ9 እስከ 12 ያለውን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ደግሞ ሰበታ ኮምፒሬሄንሲፕ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አጠናቅቀዋል። ከዛም በቅድስት ማርያም ዩኒቨርስቲ ገብተው የመጀመርያ ዲግሪያቸውን በኮምፒውተር ሳይንስ አግኝተዋል ። ሌላኛውን ዲግሪያቸውን ደግሞ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በባይሎጂ ተመርቀዋል ። ያኔ ወንድና ሴት የሚለው በትምህርት ሚኒስትር ደረጃ ካልሆነ በየትምህርት ቤቶቹ፤ በየክፍሉና በሕብረተሰቡ ዘንድ ልዩነት አልነበረውም። እንደውም ሴቶች ይበረታታሉ። መምህራኖቻቸው ከወንዶች እንዳያንሱ የሴቶች ክበብ በማቋቋም ብዙ አስተዋጾ ያደርጉላቸው ነበር። በመሆኑም በአጠቃላይ ውጤትም ሆነ በክፍል ተሳትፎ ከወንዶቹ ጋር ልዩነት አልነበራቸውም። ለመጀመርያ ጊዜ የሥራውን ዓለም የተቀላቀሉት በመምህርነት ሙያ ነው።በዚህ መካከል በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ለሦስት ወራት ሰርተዋል። ከ1997 ዓ.ም መጨረሻ ጀምረው ደግሞ አሁን እየሰሩበት ባለው የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ገብትዋል ። ከዚህ ውስጥ ከ1997 መጨረሻ እስከ 2005 ዓ.ም በዕፅዋት ማዕከል ውስጥ አገልግለዋል። ከዚህ በኋላ ደግሞ አሁን ላሉበት የኃላፊነት ቦታ ተወዳድረው አለፉ። ልምድ ባካበቱበት የወላጆቻቸው ሰዓት አጠቃቀምን ማዕከል ያደረገ የሥራ ባህል ከሚባክን ጊዜ ሰለባነት ድነው ጊዚያቸውን በአግባቡ መጠቀም ቻሉ።

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

ኃይለማርያም ወንድሙ

**በዛሬው አዲስ ዘመን ድሮ ዓምዳችን በሰላም ማስከበር ዙርያ በመተከል ወንበዴዎችን በማደን የተሠራን ሥራ ይዘን ቀርበናል፡፡ ግጥምጥሞሽ ሆኖ ዛሬም አካባቢው ሳይ አሁንም ለሚታየው ሰላም መደፍረስ ፀጥታ ኃይሉ በመናበብ መሥራት እንዳለበት የዛኔው ሰላም አስከባሪ ስራ በማሳያነት አነሳን፡፡ ሕገወጥ ንግድን በመቆጣጠርና በማኅበራዊ ሕይወት ላይ ያጠነጠኑ ዜናዎችም አዲስ ዘመን የቀድሞ ዕትሞችን ስናገላብጥ ያገኘናቸው መረጃዎች ናቸው፡፡**

### ልጅ ወልዳ የጣለች ተከሰሰች

ከተወለደ በግምት 3 ቀን ይሆነዋል ፤የተባለው ሕፃን ልጅዋን ከግንፍሌ ወንዝ ዳር ጥላ በዚሁ ምክንያት የተከሰሰችው ፀሐይ ተገኝ ወህኒ ገባች ፡፡ ዕድሜዋ ፳ ዓመት የሚሆናት ኮረዳ የወለደችውን ልጅ ከወንዝ ዳር ጥላለች በመባል የተከሰሰችው ነሐሴ ፯ ቀን ከቀኑ ፲፩ መሆኑን የአቃቤ ሕጉ ክስ ያመለክታል፡፡

ተከሳሿ የወለደችውን ልጅ ለመጣል ዋነው ምክንያት ምን እንደሆነ ከፍርድ ቤት ለቀረበላት ጥያቄ ስትመልስ ከአልባሌ ሰው በመጽነሷ ችግሯን ለመበገር ባለመቻሏ መሆኑን አመልክታለች፡፡ ፀሐይ ጳጉሜ ፫ ቀን አዲስ አበባ ከፍተኛ ፍርድ ቤት 4ኛ ወንጀል ችሎት ቀርባ ለጠበቃ የምትከፍለው የሌላት መሆኗን ብታመለክት የመንግሥት ጠበቃ እንዲከራከርላት ታዟል፡፡

ተጥሎ የተገኘው ሕፃን ሕይወቱ ካለፈ በኋላ በአንድ ተላላፊ መንገደኛ ታይቶ በአንደኛ ፖሊስ ጣቢያ አማካይነት አስከሬኑ ለምርመራ ወደ ሐኪም ቤት መላኩ ታውቋል፡፡ በጣቢያው አማካይነት በተደረገው መከታተል የጣለችው ሴት ወዲያው ተገኝታ ሁናው በምርመራ ተጣርቶ ፍርድ ቤት ቀርቧል፡፡ ተከሳሿም የነገሩ ፍሬ በፍርድ ቤት አግባብ እስቲጣራ በቀጠሮ ማረፊያ ቤት ቆይታለች ፡፡

(ጳጉሜ 4 ቀን 19 62 ከወጣው አዲስ ዘመን )

### ከመተከል 50 ወንበዴዎች በአዳኝ ቡድን ተያዙ

ደብረ ማርቆስ ፤(ኢ/ዜአ/) በመተከል አውራጃ አስተዳደር በሠፌው ሕዝብ ሕይወትና ንብረት ላይ ጉዳት ሲያደርሱ የቆዩት ፶ ወንበዴዎች ሰሞኑን ውንብድና ለማጥፋት በተሰማራው አዳኝ ቡድን ተይዘዋል፡፡

በሻለቃ አበበ ደስታ የአውራጃው ፖሊስ አዛዥ በአቶ ደስታ ተሰማ የጓንጉ ወረዳ አስተዳዳና በግራዝማች ተደሰ ጀምበሬ የሚመራው ይኸው የአዳኝ ቡድን ወንበዴዎቹን የያዘው ከሰኔ ፲፰ ቀን እስከ ፳፯ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ/ም/ ድረስ ባደረገው አደን መሆኑን በአውራጃው በተቆጣጣሪነት የተመደቡት የዐሥር አለቃ ያለው ሺበሺ ገልጠዋል፡፡

የተያዙትም ወንበዴዎች በፖሊስ ጣቢያና በወህኒ ቤት የሚገኙ ሲሆን የወንበዴዎቹ አዳኝ ቡድን አሁንም የማደን ተግባር እደቀጠለ መሆኑ የአውራጃው አስተዳዳሪ ጨምረው አስረድተዋል፡፡

( ሐምሌ 1 ቀን 19 67 ከወጣው አዲስ ዘመን ጋዜጣ)

### የሞጆ ከተማ ሕዝብ ለሥራ አጦች መጠለያ አሠራ

ናዝሬት ፤(ኢ.ዜ.አ.) በየረርና ከረዩ አውራጃ በሎሜ ወረዳ የሚገኘው የሞጆ ከተማ ሕዝብ ገንዘብና ጉልበቱን በማስተባበር ፤በከተማው ለሚገኙ ፵፱ ወዛደሮች አንድ መጠለያ ቤት ሠርቶ ማስረከቡን የወረዳው አስተዳዳሪ ገልጠዋል፡፡

ሕዝቡ ይሕንን የመጠለያ ቤት በኅብረት ሠርቶ ያስረከበው ያለ በቂ ሥራ በከተማ ውስጥ ይዘዋወሩ የነበሩን እነዚህ ፵፱ ወዝአደሮች ችግር በመመልከት መሆኑ ተገልጧል፡፡ አቶ ተስፋዬ ጣሰው የተባሉ በጎ አድራጊም ለቤቱ ክዳን የሚሆን ፪ ቆርቆሮ በግል ገዝተው መስጠታቸውን የወረዳው አስተዳዳሪ በተጨማሪ ገልጠዋል፡፡

ከዚሁም በቀር የሞጆ አካባቢ የኅብረት ማኅበር አባሎችና የወረዳው የእርሻ ሚኒስቴር ሠራተኞች ለነዚሁ ችግረኞች ወዝአደሮች ፬ ጋሻ ተኩል መሬት አርሰው ማስረከባቸውን ተገልጧል፡፡

(መስከረም 8 ቀን 1968 የወጣው አዲስ ዘመን ጋዜጣ)

### ሁለት ሕገወጥ ነጋዴዎች 5500 መቀጫ ተፈረደባቸው

ድሬ(ኢ.ዜ.አ) በድሬ ከ፬ የታወቁ ነጋዴዎች ከተወሰነው ዋጋ አስበልጠው በመሸጥና የመብል ዘይት የንግድ ሚኒስቴር ያልመዘገበውን የምግብ ዘይት ለሕዝቡ በማከፋፈል በቀረበባቸው ክስ 5500 ብር መቀጫ እንዲከፍሉ የድሬዳዋ 3ኛ ወንጀል ፍርድ ቤት ትናንት ፈረደ፡፡

ከተቀጡት ነጋዴዎች ውስጥ ሐጂ ሙሜ አህመድ የተባሉት ከድሬዳዋ ጥጥ ኩባንያ በውክልና አንድን ኪሎ ቁርጥራጭ ጨርቅ በ0.75 ሳንቲም ከተረከቡ በኋላ ለአነስተኛ ነጋዴዎች አንድን ኪሎ ቁርጥራጭ ጨርቅ ከ6 ብር እስከ 10 ብር እየሸጡ ብዙ ዓመት ሲጠቀሙ በመቆየታቸው በአነስተኛ ልብስ ሰፊዎች አመልካችነት በድሬዳዋ አውራጃ አስተዳዳሪ በአቶ ሳሙኤል ተፈሪ አማካይነት ጉዳዩ ከሕግ ፊት ቀርቦ በማስረጃ ስለተረጋገጠባቸው 3000 መቀጫ እንዲከፍሉ ተወስኖባቸው ገንዘቡን ወዲያውኑ ከፍለዋል፡፡

ሐጂ በዚህ ሥራ መጠቀም የጀመሩት እንደ አውሮፓውያን ዘመን አቆጣጠር ከ1964 ዓ.ም ጀምሮ መሆኑን ፍርድ ቤቱ ባዘጋጀው የፍርድ ሀተታ ገልጦ፤የድሬዳዋ ጥጥ ኩባንያ ግን ተከሳሹ እስካሁን ምን ያህል ኪሎ ጨርቅ እንደወሰዱና ምንያህል ጥቅም እንዳገኙበት ሲጠየቅ ‹‹ለዚህ የተለየ መዝገብ የለንም›› በማለት ሳይገለጥ መቅረቱ ተገልጧል፡፡

እንደዚሁም አቶ ያኒዮር ጋሲት የተባሉ ድሬዳዋ የሚገኘው የዘይት ፋብሪካ ባለቤት ለቸርቻሪ ነጋዴዎች ፩ን ኪሎ የመብል ዘይት በ፩ ብር ከ፳፭ ሳንቲም ማከፋፈል ሲገባቸው ብር ከ፹፬ ሳንቲም በመሸጣቸውና ንግድ ሚኒስቴር ያልመዘገበውን የዘይት ዓይነት ሠርተው ዋጋውን ሳይተምኑ ፩ን ኪሎ በ፪ ብር ፴፭ ሳንቲም ሲሸጡ በተቆጣጣሪዎች ተደርሶባቸው ለቀረበባቸው ክስ በምስክርና በማስረጃ ስለተረጋገጠባቸው ፍርድ ቤቱ ትናንት ባዋለው ችሎት ፪ሽህ፭፻ ብር መቀጫ እንዲከፍሉ ወስኖባቸው ተከሳሽም ገንዘቡን ወዲያውኑ ከፍለዋል፡፡

ተከሳሹ ሊሸጥ ከሚገባው በላይ በመሸጥ በጥር ፩ ቀን ፳፯ ዓ/ም/ ፵፩ ሽህ ፫፻፴፫ብር ከ፳፫ ሳንቲም ማግኘታቸውን በፍርድ ቤቱ በፍርድ ሀተታቸው ተገልጧል፡፡

(ሰኔ 26 ቀን 1967 ከወጣው አዲስ ዘመን )

# ዓለም አቀፍ

## ዩኬ በአንዳንድ ስደተኞች ላይ የኤሌክትሮኒክስ መለያ ልትገጥም ነው

በጋዜጣው ሪፖርተር

በአነስተኛ ጀልባዎች ወይም በጭነት መኪኖች ወደ ዩናይትድ ኪንግደም የገቡ አንዳንድ ጥገኝነት ጠያቂዎች የኤሌክትሮኒክስ መለያ ሊገጠምላቸው መሆኑ ተገልጿል።

የአገር ውስጥ ሚኒስቴር ሙከራ አካል ነው የተባለው እርምጃ መንግሥት አደገኛ ወይም አላስፈላጊ በሚላቸው መንገዶች የገቡና የሚባረሩ ስደተኞችም ላይ ለ12 ወራት ያህል እንደሚተገበር ተገልጿል።

ቦሪስ ጆንሰን "ጥገኝነት ጠያቂዎች ወደተቀረው የአገሪቱ ክፍል መጥፋት እንደማይችሉ ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው" ብለዋል። ተቺዎች በበኩላቸው ይህ እቅድ ስደተኞችን እንደ ወንጀለኞች የሚመለከት ነው ሲሉ ወቅሰዋል ሲል ቢቢሲ ዘግቧል።

ይህ ጅማሮ ከእንግሊዝ ወደ ሩዋንዳ ጥገኝነት ጠያቂዎችን ለማጓጓዝ ሊደረግ የነበረው የመጀመሪያው በረራ በአውሮፓ የሰብአዊ መብቶች ፍርድ ቤት የመጨረሻ ደቂቃ ጣልቃ ገብነት ከተሰረዘ ከጥቂት ቀናት በኋላ ነው።



የመጀመሪያው የኤሌክትሮኒክ መለያ የሚገጠምላቸው ያንን በረራ በተሳካ ሁኔታ እንዳይሳካ የተሟገቱ የሆኑ ሰዎች ሊሆኑ ይችላሉ።

የሃገር ውስጥ ጽሕፈት ቤት በእንግሊዝ እና በዌልስ የጀመረው የኤሌክትሮኒክስ መለያ መግጠም ጥገኝነት ጠያቂዎች ሂደታቸው በብቃት እንዲከናወን ሊረዳ ይችላል ወይ የሚለውንም እንደሚፈትሽ አስታውቋል።

ምንም እንኳን ሙከራው የተጀመረ ቢሆንም፣ የአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር እስካሁን የኤሌክትሮኒክስ መለያ ተገጥሟል ስለሚለው ምንም አይነት አስተያየት አልሰጠም።

መለያ የተገጠመላቸው ስደተኞች የሰዓት እላፊ ገደብ ሊጣልባቸው ይችላል እንዲሁም የተሰጧቸውን ትዕዛዞች የማያከብሩ ከሆነም ወደ እስር ቤት ሊወሰዱ ወይም ሊከሰሱ ይችላሉ።

መመሪያው ከዩናይትድ ኪንግደም እንደሚባረሩ የተነገራቸው ስደተኞች ሊሸሹ ይችላሉ እንዲሁም የኢሚግሬሽን የዋስትና ሁኔታዎችን ላያከብሩ እንደሚችሉም አትቷል።

ከስደተኞች ጋር የሚሰሩ ሰራተኞች መሳሪያው በሰውዬው አእምሮአዊ ወይም አካላዊ ጤንነት ላይ ከባድ ጉዳት ያደርስ እንደሆነ ወይም የስቃይ ወይም የዘመናዊ ባርነት ሰለባ መሆን አለመሆኑን ማጤን አለባቸው። የሆም ኦፊስ መመሪያ ህጻናትን ወይም እርጉዝ ሴቶችን አይጨምርም ይላል።

## በሕንድ እና ባንግላዲሽ በርካቶችን የገደለው ጎርፍ ሚሊዮኖችን መውጫ አሳጥቷል ተባለ

በጋዜጣው ሪፖርተር

በሕንድ እና ባንግላዲሽ ከባድ ዝናብ ባስከተለው የመብረቅ እና የመሬት መንሸራተት አደጋ ቢያንስ 59 ሰዎች ሞቱ። የአደጋ መከላከል ሠራተኞች መውጪያ ያጡ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎችን ለመታደግ በርብርብ ላይ ናቸው።

የጎርፉ መጠን በመጪዎቹ ቀናት አሁን ካለው በላይ የከፋ ሊሆን እንደሚችል ተገምቷል። የባንግላዲሽ መንግሥት አሁን ያለው ጎርፍ እንደ አውሮፓውያኑ ከ2004 ወዲህ እጅግ የከፋው ነው ሲል ገልጾታል።

ባለፈው ሳምንት የተከሰተው ከባድ ዝናብ የአገሪቱን ሰሜናዊ ምሥራቅ ተራራማ አከባቢዎችን አካሎ ጎረቤቷ ሕንድ ላይም ጉዳት አስከትሏል። በአካባቢዎቹ ትምህርት በጊዜያዊ መጠለያዎች እንዲሰጥ እየተደረገ ሲሆን ጎርፉ ባስከተለው የውሃ ሙላት ግንኙነት የተቋረጡባቸው ነዋሪዎችን ለመታደግ ወታደሮች በስፍራው ተሰማርተዋል።

ኮምፓኒጋኒ በተባለው ስፍራ የሚኖር ግለሰብ "እስከ ባለፈው አርብ ጠዋት አካባቢው በሙሉ በውሃ ተጥለቅልቆ ነበር። ሁላችንም መውጫ አጥተን ተቸግረን ነበር" ሲል አስተያየቱን ለኤኤፍፒ ሰጥቷል።

"ቀኑን ሙሉ በቤታችን ጣሪያ ላይ ቆይተን ጎረቤቶቻችን በሠሩት ጊዜያዊ ጀልባ ከአደጋው ተርፈናል። እናቴ በሕይወቷ እንዲህ ዓይነት አደጋ አይታ እንደማታውቅ ነግራኛለች" ሲል አክሏል የ23 ዓመቱ አስተያየት ሰጪ።

ሌላ ከጎርፍ አደጋው የተረፈች ሴት ደግሞ ለሁለት ቀናት ምግብ መመገብ እንዳልቻለች ተናግራለች። "የውሃ ሙላቱ የተከሰተው በጣም በፍጥነት ነው። በዚህም ምክንያት ያለንን ነገር ይዘን መውጣት አልቻልንም። ሁሉ ነገራችንን ውሃ ውስጥ ሆነን እንዴት ማብሰል እንችላለን" ስትል አስተያየቷን ለዜና ወኪሉ ሰጥታለች።

በጎረቤቷ ሕንድ አሳም በተሰኘችው ግዛት አንድ ነጥብ ስምንት ሚሊዮን የሚሆን ሰው ለአምስት ቀናት በጣለው ተከታታይ ከባድ ዝናብ ምክንያት በተለያየ መንገድ ተጎጂ መሆናቸው ተሰምቷል። የግዛቲቱ አስተዳዳሪ ሂማንታ ቢስዋ ሳርማ በጎርፉ ተይዘው ላሉ ነዋሪዎች አስፈላጊው እርዳታ እንዲቀርብ ማዘዛቸውን ለጋዜጠኞች ተናግረዋል።

ባንግላዲሽ በዚህ ሳምንት በዚህ አደጋ ከመጠቃቷ በፊት ሲለት የተባለችው ግዛቷ ላይ ከሁለት አስርት ዓመታት ወዲህ የከፋ ነው የተባለውን አደጋ ባለፈው ወር አስተናግዳ ነበር። በአደጋው ቢያንስ 10 ሰዎች ሲሞቱ አራት ሚሊዮን የሚሆኑ ሰዎች ተጎጂ ሆነዋል። ታዲያ አገሪቱ ከዚህ አደጋ ገና በማገገም ላይ ሳለች ነው የዚህ ሳምንት አደጋ የተከሰተው።



በባንግላዲሽ ሕግ አውጪ የነበረ ሰይድ ራፊኩል አገሪቱ ቀደም ብላ በሰብአዊ ቀውስ ውስጥ እንደነበረች ተናግሯል። "ሙሉ ለሙሉ በሚባል ደረጃ የሲለት ግዛት ዙሪያ በውሃ ውስጥ የነበረ ሲሆን፤ በሚለዮን የሚቆጠሩ ሰዎች መውጫ አጥተው ነበር " ሲል ለሮይተርስ አስተያየቱን ሰጥቷል።

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
ዘመን
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጻችንንና ፊስቡክ ገጻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

አዲስ ዘመን

ማክሰኞ

# ስፖርት



ይህ ቦታ ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# ዋልያዎቹን ከስደት የማያድነው ተስፋ አስቆራጭ ጥረት

ቦጋለ አበበ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን(ዋልያዎቹ) ከሳምንት በፊት በ2023 የአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ የምድብ አራት ሁለት ጨዋታዎችን አከናውነዋል። ኢትዮጵያ አለም አቀፍ ጨዋታዎችን ለማስተናገድ የካፍን ዝቅተኛ መስፈርት የሚያሟላ ስቴድየም የሌላት መሆኑን ተከትሎ ዋልያዎቹ ከሁለቱ አንዱን የማጣሪያ ጨዋታ በሜዳቸው ማድረግ ሲገባቸው በገለልተኛ አገር ለማከናወን መገደዳቸው ይታወቃል። ዋልያዎቹ ከሜዳቸው ውጪ የመጀመሪያውን ጨዋታ ከማላዊ አቻቸው ጋር ሊሎንዌ ቤንጉ ስቴድየም አድርገው 2ለ1 ቢሸነፉም በጨዋታው ያሳዩት አስደናቂ እንቅስቃሴ አድናቆትን አትርፎላቸዋል። በዚህ ጨዋታ ካገኙት አድናቆት ባለፈም በተመሳሳይ አገርና ስቴድየም የአህጉሪቱን ትልቅ ብሔራዊ ቡድን ግብጽን በቀናት ልዩነት 2ለ 0 በማሸነፍ የኢትዮጵያን ሕዝብ ማስደሰት ችለዋል። ዋልያዎቹ ይህን ታላቅ ጨዋታ በፍጹም የበላይነት ማሸነፍ ቢችሉም ድሉን በሜዳቸው ከደጋፊያቸው ጋር ሆነው ማጣጣም አለመቻላቸው የስፖርት ቤተሰቡን ቁጭት ውስጥ ከቷል።

ከእግር ኳስ በዘለለ ብዙ ትርጉም ያለው የዋልያዎቹ ድል በጅምር የቀሩ በርካታ የኢትዮጵያ ስቴድየሞችን ጉዳይ ከተዳፈነበት ቀስቅሷል። “ከመቶ ሚሊየን በላይ ሕዝብ ያላት አንድ ታላቅ አገር እንዴት አንድ የካፍን ዝቅተኛ መስፈርት የሚያሟላ ስቴድየም አይኖራትም?” የሚለው ጥያቄ ከዋልያዎቹ ድል ጎን ለጎን በስፋት መወያያነቱ አሁንም ቀጥሏል። ይህ ጥያቄ የሀገር ውስጥ መገናኛ ብዙሃን የየእለት አጀንዳም ሆኗል። እግር ኳስ አፍቃሪው ማህበረሰብ ብቻ ሳይሆን ለስፖርት ግድ የሌለው ጭምር ይህን ጥያቄ በመቆጨት ስሜት እየጠየቀና እየተወያየም ይገኛል። ኢትዮጵያውያንን በአንድ ያስማማው የዋልያዎቹ ድል በቀጣይ የማጣሪያ ሁለት ጨዋታዎች



**የአዲስ አበባ ስቴድየም የመጫወቻ ሜዳ የሳር መትከል ስራ ብዙዎችን እያነጋገረ ይገኛል፣**

ቡድኑ ፍልሚያዎችን በሜዳው እንዲያደርግ የሚመለከተው አካል ጥረት እንዲያደርግም ጥያቄው ዛሬም ቀጥሏል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየተገነባ የሚገኘውን የአደይ አበባ ብሔራዊ ስቴድየም በአጭር ጊዜ እንዲጠናቀቅ ጥረት እያደረገ እንደሚገኝ በተደጋጋሚ የሚገልጸው የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር፣ በተጨማሪም እየታደሰ የሚገኘው አንጋፋው የአዲስ አበባ ስቴድየም ዋልያዎቹ በቀጣይ መስከረም ለሚጠብቃቸው ፍልሚያ እንዲደርስ ጥረቱን እንደሚቀጥል ሲገልጽ ቆይቷል። ለዚህ ጥረቱ ማሳያም ባለፈው አርብ የአዲስ አበባ ስቴድየምን የመጫወቻ ሜዳ የሳር ማንጠፍ ስራ እንደጀመረ በማህበራዊ ትስስር ገጹ በፎቶ ግራፍ አስደግፎ ያወጣው መረጃ ጠቁሟል። የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በዚህ ረገድ ስለቀጣዩ የዋልያዎቹ ፍልሚያ ተጨንቆ ስቴድየሙን ብቁ ለማድረግ ያሳየው ተነሳሽነትና ጥረት ሳይደነቅ አይታለፍም። ሆኖም ጥረቱ ያለውን ችግር በአጭር ጊዜ ለመፍታት የሚበቃ እንዳልሆነ እየተከናወኑ ከሚገኙ ስራዎች መገንዘብ ይቻላል።

የአዲስ አበባ ስቴድየም መጫወቻ ሜዳ የሳር ማንጠፍ ስራ እየተከናወነ የሚገኘው በጣት በሚቆጠሩ ሰዎች ኋላ ቀር በሆነ መንገድ መሆኑን ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ጥረቱን እዩልኝ ብሎ በማህበራዊ ትስስር ገጹ ያጋራው ፎቶ ግራፍ ምስክር ነው። ካፍ የኢትዮጵያ ስቴድየሞች ቢያንስ ዝቅተኛ መስፈርት ማሟላት አለባቸው ብሎ በእግር ኳስ ፌዴሬሽን ያቀረበው ባለ ዘጠኝ ገጽ ምክረ ሃሳብ በዋናነት የእግር ኳስ መጫወቻ ሜዳውን የሚመለከት ነው። ይህም የመጫወቻ ሜዳው የሳር ማንጠፍ ስራ ሲከናወን በሙያው ከካፍና ከፊፋ እውቅና የተሰጣቸው ተቋማት አማካሪ መሆን እንዳለባቸው ያስቀምጣል። በሳር ማንጠፉ ስራ ብቻ ሳይሆን ሳሩ ከተነጠፈ በኋላም በሙያው የተካኑ አማካሪ ተቋማት ሜዳውን በመንከባከብ ረገድ አስፈላጊ መሆናቸውን ካፍ በምክረሃሳቡ በዝርዝር አስቀምጧል።

አሁን የአዲስ አበባ ስቴድየም የሳር ማንጠፍ ስራ እየተከናወነ የሚገኘው ግን ከዚህ ከካፍ ምክረ ሃሳብ በተቃራኒ ስለመሆኑ በግልጽ እየታየ ነው። በቀደሙት በርካታ አመታት ሲደረግ እንደነበረው በተወሰኑም ይሁን በበርካታ ሰዎች እንደማንኛውም የመጫወቻ ሜዳ የሳር ነጠፋ ስራው ተከናውኖ ካፍን እንዴት ማሳመን እንደሚቻል መልስ ያላቸው ስራውን የሚያከናውኑት ብቻ ናቸው። እርግጠኛ ሆኖ መናገር የሚቻለው ግን አሁን እየተሰራ ባለው መንገድ ካፍን አሳምኖ በመጪው መስከረም የአዲስ አበባ ስቴድየም ለዋልያዎቹ ጨዋታ ብቁ ማድረግ እንደማይቻል ነው።

የአዲስ አበባ ስቴድየም ይህን የመጫወቻ ሜዳ በተመለከተ የካፍን ይሁንታ ያገኛል ብለን ብናምን እንኳን የመታጠቢያና መጸዳጃ ቤቶች፣ለመገናኛ ብዙሃን መግለጫ የሚሰጥበትን አዳራሽ የተመለከቱ ጉዳዮችን እንዴት መስፈርቱን አሟልተው የካፍ ይሁንታ እንደሚገኝ ለብዙዎች ግራ ነው። በአጭሩ ዋልያዎቹ ቀጣዮቹን ጨዋታዎች በሜዳቸው የማድረጋቸው ጉዳይ ያከተመለት ነው ብሎ በድፍረት ሳይሆን ካለው ነባራዊ ነገር ተነስቶ መደምደም ይቻላል።

ዋልያዎቹ ቀጣዮቹን ጨዋታዎች በአገራቸው ለማድረግ ትንሽም ቢሆን ተስፋ የነበረው የአዲስ አበባ ስቴድየም ነበር። ሆኖም “የማያጠግብ እንጀራ ከምጣዱ ያስታውቃል” እንደሚባለው የስቴድየሙ እድሳት በተለይም ዋናው የመጫወቻ ሜዳ የሳር ማንጠፍ ስራ ከዘመኑ ጋር እየተራመደ አለመሆኑ ያለውን ተስፋ የሚያጨልም ሆኗል።

የአደይ አበባን ብሔራዊ ስቴድየምን በተመለከተ ለዋልያዎቹ የመስከረም ጨዋታ ይደርሳል ብሎ ተስፋ የሚያደርግ አይኖርምና የእሱ ጉዳይ ይቆይ። ሌላው የተሻለ ተስፋ ተጥሎበት የነበረው የባህርዳር ስቴድየምም ቢሆን ከላይ ሲመለከቱት በጥሩ ቁመና ላይ የሚገኝ ይምሰል እንጂ በአጭር ጊዜና ገንዘብ ለካፍ መስፈርት ብቁ የማያደርጉት በርካታ መሟላት ያለባቸው ችግሮች እንዳሉበት የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ዋና ጸሐፊ አቶ ባህሩ ጥላሁን ባለፈው መግለጫ ላይ ጠቁመው ነበር።

ኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን
Ethiopian Cooperative Commission

## ከኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# “ኅብረት ሥራ ማህበራት ለተሻለች ኢትዮጵያ” 14ኛው ዓለም አቀፍ የኅብረት ሥራ ቀን

በአለምነህ ቸርነት

የዓለም ኅብረት ሥራ ቀን በዓለምአቀፍ ደረጃ ሲከበር ዘንድሮ መቶኛ ዓመት ያስቆጠረ ሲሆን የተባበሩት መንግሥታት እና የዓለም ኅብረት ሥራ ድርጅት በጋራ የዓመቱን መሪ ቃል እያዘጋጁ በይፋ ማክበር ከጀመሩ ደግሞ እነሆ 28ኛ ዓመት ላይ ደርሷል።በሀገራችን የዓለም ኅብረት ሥራ ቀን መከበር ከጀመረበት ከ2001 ዓ.ም ጀምሮ ዛሬ 14ኛው ዓመት ላይ የምንገኝ ሲሆን በእነዚህ ዓመታት ዕለቱ በተለያዩ የተመረጡ መሪ ቃሎች ሲከበር ቆይቷል።

በዚህም መሰረት 14ኛው ሀገር አቀፍ የኅብረት ሥራ ቀን ክብረ በዓል “ኅብረት ሥራ ማህበራት ለተሻለች ኢትዮጵያ” በሚል መሪ ቃል ሰኔ 10 ቀን 2014 ዓ.ም በሀገራችን ተከብሯል። ዘንድሮ ይህን መሪ ቃል ተንተርሶ ሀገር አቀፍ የኅብረት ሥራ ቀን የተከበረው ኢትዮጵያ የገጠማትን ወቅታዊ ችግር ተከትሎ ኢኮኖሚያዊ ተፅእኖዎችን እንድትቋቋም ኅብረት ሥራ ማህበራት የራሳቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ለማስቻል ነው።በዚህም ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ መርሃ ግብሩን ተግባራዊ በማድረግ በተለይም የግብርና ምርታማነትን በእጥፍ በማሳደግ የምግብ ዋስትናችንን ለማረጋገጥ በትኩረት መሥራት እንደሚያስፈልግ የጋራ አቋም በመያዝ መንቀሳቀስ ተጀምሯል።

ዓለማችን አሁን ባለችበት የፖለቲካ ውጥረትና ጦርነት ኢኮኖሚዋ በእጅጉ ተዛብቷል። በመላው ዓለም የምግብ ሰብል ምርትና የሸቀጦች ዋጋ በእጅጉ አሻቅቧል።እንደ ነዳጅና ማዳበሪያ ያሉ ምርቶች ዋጋቸው የማይቀመስ ሆኗል።በዚህም ምክንያት ዓለማችን በሰብል ምርትና ሸቀጥ ግብይት ቀውስ እየታመሰች ትገኛለች።ከዚህ አንጻር ኅብረት ሥራ ማህበራት ገበያን በማረጋጋት ሂደት እያበረከቱ ያለው አስተዋጽኦ ቀላል ግምት የሚሰጠው አይደለም።

ኅብረት ሥራ ማህበራት ምርትና ሸቀጥን ከውጭ በማስገባት የህዝቦችን ኑሮ ለመደጎም ጥረት ቢያደርጉም በአፍሪካ ያለው ኢኮኖሚያዊ ቀውስ በከፍተኛ ደረጃ እየተባባሰ በመምጣቱ ጉዳዩን በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ አድርጎታል። ሀገራችን ጦርነት፣ ግጭት፣ አለመረጋጋትና ውጥረት ውስጥ እንደመከረሟ መጠን ኢኮኖሚያዊ ቀውሱን በአያሌው አክብዶታል።ጥናቶች እንደሚያመላክቱት ዓለም አቀፍ ውጥረቱ / በተለይም የዩኩሬንና የሩሲያ ጦርነት/ በኢኮኖሚው ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ በቀጣይ አምስት ዓመታት ጭምር የሚቀጥል በመሆኑ ችግሩን እንደሚያባብሰው ይገመታል። የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ አንቶኒዮ ጉተሬዝ ዓለማችን ያለችበትን ተጨባጭ ሁኔታ ሲያስረዱ “ዓለማችን መውጣት ከሚያዳግታት አዘቅት ውስጥ ተዘፍቃለች...በተሳሳተ መንገድ እየነጎደች ነው... ስለዚህ ተስፋችን እንዲያንሰራራ መተባበር ያስፈልገናል፣ መነጋገር ያስፈልገናል፣ መግባባት ያስፈልገናል።” ብለዋል።

ሰው ተኮር የሆነው የኅብረት ሥራ የቢዝነስ ሞዴል ኃላፊነትን መወጣት፣ ዲሞክራሲ፣ እኩልነት፣ ፍትሃዊነት፣ አንድነት፣ ለሌሎች ማሰብ በመሳሰሉ እሴቶቹ ፍትሃዊ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት እንዲኖር የሚሠራ በመሆኑ አሁን ካለንበት ፈተና ለመውጣት የመፍትሄ አካል እንደሚሆን ይታመናል።

በመሆኑም በዚህ ሀገር አቀፍ የኅብረት ሥራ ቀን እያደገ የመጣው የግብርና ምርትና ሸቀጥ አቅርቦት እጥረትና ግሽበትን ለመቋቋም አርሶ አደሮቻችንና ኅብረት ሥራ ማህበራት ከተለምዷዊው የምርታማነት አቅማቸው በእጅጉ ጠንክረው ከፍተኛ የግብርና ምርታማነት ለማምጣት ብርቱ ሥራ እንደሚጠብቃቸው በአጽንኦት ተንጸባርቋል። ምርታማነትን ለማሳደግ የተፈጥሮ የአፈር ማዳበሪያን በአማራጭነት መጠቀም በትኩረት ሊታይ እንደሚገባም ተገልጿል፡፡

ሀገራችን በአመዛኙ ኢኮኖሚዋ የተመሰረተው በግብርና ላይ እንደመሆኑ የግብርና ኅብረት ሥራ ማህበራት ሀገራችን ያላትን ዕምቅ አቅም አሟጠው በመጠቀም በስንዴ የተጀመረውን ምርታማነት ወደ ሌሎች የምግብ ሰብል ምርቶች በማስፋት ምርታማነትን በማሳደግ ከሀገር በዘለለ ምርትን ኤክስፖርት በማድረግ የወቅቱን ፈተና ወደ እድል ለመቀየር የላቀ አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ መልዕክት ተላልፏል።እ.አ.አ. ሐምሌ 2 ቀን 2022 በመላው ዓለማችን የሚገኙ ኅብረት ሥራ ማህበራት መቶኛውን የዓለም ኅብረት ሥራ ቀን “ኅብረት ሥራ ማህበራት ለተሻለች ዓለም” /Cooperatives Build a Better World በሚል መሪ ቃል የሚያከብሩት ይሆናል።የዘንድሮው የዓለም ኅብረት ሥራ ቀን በዚህ ማጠንጠኛ መሪ ቃል እንዲከበር የተመረጠበት ዋናው ምክንያት ኅብረት ሥራ ማህበራት ዓለማችን የተሻለች መኖሪያ እንድትሆን ያደረጉትን ልዩ አስተዋጽኦ ለመዘከር ታልሞ ነው።ያም ብቻ ሳይሆን አሁን ዓለም የገጠማትን የኢኮኖሚ ፈተና ለማረጋጋት የኅብረት ሥራ ማህበራት ሚና ትልቅ በመሆኑ ነው።

ኅብረት ሥራ ማህበራት በጋራ ስነምግባራዊ እሴቶች ላይ በተመሰረቱ ዓለም አቀፋዊ ስምምነት ባላቸው መርሆዎች የሚመሩ ብቸኛ ተቋም ናቸው።ኅብረት ሥራ ማህበራት በቀውስ ውስጥ ተፈጥረው ቀውስን የሚታደጉ ተቋማት መሆናቸው ታሪካዊ ዳራቸው ያሳያል። በዚህም መሰረት ባለፉት ዘመናት በዓለማችን ለተከሰቱ የተለያዩ ቀውሶች ኅብረት ሥራ ማህበራት ምላሽ በመስጠት አስፈላጊነታቸውንና አይበገሬነታቸውን አስመስክረዋል። የማህበረሰብ ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎን አፋጥነዋል።የአካባቢ መራቆትንና የአየር ንብረት ለውጥን መክተዋል። በርካታ የሥራ እድሎች ፈጥረዋል።ለምግብ ዋስትና መረጋገጥ አስተዋጽኦ አበርክተዋል።በየአካባቢው ላለው ማህበረሰብ የፋይናንስ አቅርቦት እንዲኖር አግዘዋል። ስነምግባርን የተከተለ የእሴት ሰንሰለት እንዲፈጠር አድርገዋል።እንዲሁም የሰዎች ቁሳዊ ፍላጎትንና የደህንነት ሁኔታን በማሻሻል ለአዎንታዊ ሰላም አስተዋጽኦ አበርክተዋል።ከዚህ አንጻር አሁን የዓለምንም ይሁን የሀገራችንን ወቅታዊ አለመረጋጋት ተከትሎ በኢኮኖሚው ላይ የተፈጠረውን ጫና ለማርገብ ኅብረት ሥራ ማህበራት ከመቼውም ጊዜ በላይ ተልእኳቸውን በመወጣት ህብረተሰቡን ማገዝ የሚጠበቅባቸው ወሳኝ ሰዓት ላይ ይገኛሉ።

**አድራሻ | የፌዴራል ኅብረት ሥራ ኮሚሽን | 0115573448/ 0118592105 | ፖ.ሳ.ቁ. 19787 | Facebook: Federal cooperative Agency | Website: www.fca.gov.et**

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ